# የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

## ትምህርት ሦስት

# ኢየሱስ ክርስቶስ

## The Apostles' Creed
## Lesson Three
## Jesus Christ

ተርጓሚ፥ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

## ማውጫ


# 1. መግቢያ

# 2. መለኮት

የእግዚአብሔር ልጅ

ጌታ

# 3. ሰውነት

ልምዶች

- ትውልድ
- አካል
- ነፍስ
- ትንሣኤ

ቢሮ/ አገልግሎት

- የብሉይ ኪዳን ዳራ
- ምልአት በኢየሱስ

ማንነት

# 4. ሥራ

ትኅትና

- ትስጉት
- ህማም

ክብር

- ትንሣኤ
- ዕርገት
- መንበረ ንግሥና
- ፍርድ

# 5. ማጠቃለያ

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ  አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# 1. መግቢያ

ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት፣ ቢሊዮኖች አምልከውታል፣ ተከትለውታል የናዝሬቱ ኢየሱስንም ወንጌል አውጀዋል፡፡ በታሪክ ውስጥ የእርሱን ያክል በማኅበረሰቡ ውስጥ በስፋት የተደነቀ ወይንም ተፅዕኖ ያሳደረ ሰው የለም፡፡ የስነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ ሙዚቀኞች እና ፀሐፍት የጥበባቸው ረዕሰ ጉዳይ አድርገውታል፡፡ መንግሥታትና ባህሎችም በእርሱ አስተምህሮ ዙሪያ ተመሥርተዋል፡፡ በበርካታ የዓለም ክፍሎች አገልግሎት የሚሰጡ የቀን መቁጠሪያዎች ከእርሱ ልደት በመጀመር ነው የሚቆጥሩት፡፡

ሆኖም ኢየሱስ በውል የመታወቁን ያህል፣ በጥንቃቄ የሚመረመር ርዕሰ ጉዳይም ነው፡፡ የየትኛውም ዓይነት ምሁራን መርምረውታል፡፡ ከሃዲዎች ዋጋቢስ ሊያደርጉት ይጥራሉ፡፡ ተከታዮቹ ደግሞ ሊታሰብ በሚቻለው መጠን ያጠኑታል፡፡

እንግዲህ እውነታው ለሰው ዘር ሁሉ ስለ ኢየሱስ ማጥናት እጅግ ወሳኝነት አለው፣ ምክንያቱም አንድ ቀን “ኢየሱስ ማነው?” ለሚለው ጥያቄ መልስን እንሰጣለን፡፡ ለክርስቲያኖች መልሱ የታወቀ ነው፣ ምክንያቱም ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስንከልሰው ኖረናልና፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ከተሰኘው ተከታታይ ርዕሳችን ይህ ሦስተኛው ትምህርት ሲሆን፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ” የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ ትኩረታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን፣ የእግዚአብሔርን ልጅ፣ የስላሴን ሦስተኛ አካል ወደሚያረጋግጥልን ወደ እምነት አንቀጻችን እናዞራለን፡፡ አንቀፁም እንደሚከተለው ይነበባል፡

*… በአንድ ልጁ፣*  
*በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣*  
*ከድንግል ማርያም በተወለደ፣*  
*በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣*  
*በተሰቀለ፣ በሞተ እና በተቀበረ፤*  
*ወደ ሲዖልም በወረደ፡፡*  
*በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፡፡*  
*ወደ ሰማይም በወጣ*  
*ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣*  
*ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ፣*  
*በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡*

የሃይማኖት መግለጫው ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን ማጠቃለል የሚቻልበት በርካታ መንገድ ቢኖርም፣ በነገረ-መለኮት ታሪክ ውስጥ የጋራ የትኩረት ነጥቦች በሆኑት ሦስት መሪ ሃሳቦች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት እንነጋገራለን፣ ማለትም ስለመለኮትነቱ እና ከሌሎቹ የስላሴ አካላት ጋር ስላለው ግንኙነት ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ሰውነቱ እንመለከታለን፣ በዚህም በመለኮትነቱና በሰውነቱ መካከል ያለውን ግንኙነት እናነሳለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ስለ ሥራው እንነጋገራለን፣ በምድር የአገልግሎቱ ዘመን ስለነበረው ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያም በኋላ ስላለው እናነሳለን፡፡ አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በምን መንገድ እንደተገለጠ በመመልከት እንጀምር፡፡

## 2. መለኮትነት

> *ስለ ክርስቶስ መለኮትነት ስንነጋገር፣ ወይም በተሻለ አግባብ፣ ስለ አምላክነቱ ስንነጋገር ማለትም እርሱ ፍፁም አምላክ የመሆኑን እውነታ ስንጋገር አዲስ ኪዳን ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚያነሳውን ማረጋገጫ ማለታችን ነው፡፡ የተነገረንም ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍፁምም ሰው መሆኑን ነው፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ዘወር ባልንበት ቅጽበት ኢየሱስ የለንም ማለት ነው፡፡ ኢየሱስን ከአምላክነቱ አንፃር ልንገልጥ የምንችልበት ብቸኛ መንገድ መጽሐፍ ቅዱሱ በገለጠው መንገድ ብቻ ነው፡፡ እርሱም የነገረን እርሱ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ነው፡፡ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ይሰበክ የነበረው መሠረታዊ እውነታ ይህ ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ከፃፈው እንደምንመለከተው ያለን ዋስትና ኢየሱስ በሁሉም ላይ ትልቅ ሥልጣን ያለው መሆኑ ነው፡፡ ሁሉም በእርሱ ተፈጥሯል፡፡ ሥልጣን ሁሉ በእግሩ ስር ይሰግዳል፡፡ ይህም የተነገረው ለአምላክ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ካወጣን፣ ወንጌል የለንም፣ ኢየሱስም የለንም ክርስትና ብሎ ነገርም የለም፡፡ [ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር፣ ዳግማዊ]*

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ስለ ኢየሱስ መለኮትነት የሚያነሳው በእነዚህ ቃላት ነው፡

> *…በአንድ ልጁ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡*

ክርስቲያኖች ዘወትር “ክርስቶስ”፣ “የእግዚአብሔር ልጅ” እና “ጌታ” የሚሉትን ቃላት ለኢየሱስ መለኮትነት ይጠቀማሉ፡፡

ለአሁኑ  ዓላማችን ግን፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የኢየሱስን መለኮትነት ለማመልከት በተጠቀመባቸው ሁለት ቃላት ላይ ብቻ  እናተኩራለን፡፡ በአንድ ወገን፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑን እውነታ እንመለከታለን፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ፣ ኢየሱስ ጌታ ነው ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመረምራለን፡፡ እስኪ ቅዱሳት መጻሕፍት ለኢየሱስ የተጠቀሙበትን "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለውን ቃል ፍቺ በመመልከት እንጀምር፡፡

# የእግዚአብሔር ልጅ

"የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለውን ቋንቋ አስመልክቶ ልናስታውሰው የሚገባ የመጀመሪያ ነገር ይህንን ቃል መለኮትነት ለሌላቸውም አካላት ጭምር ቅዱሳት መጻሕፍት ተጠቀመውበት እንደነበር ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ  ኢዮብ ምዕራፍ 1 ቁጥር 6 እና ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 ያሉትን ምንባቦች ስንመለከት መላእክት የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ በጥቂት ዘመናውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች፣ ጥቅሶቹ የእግዚአብሔር ልጆች ከማለት ይልቅ "መላእክት" ተብለው ተተርጉመዋል፡፡ በኢዮብ ውስጥ በሚገኙት ምንባቦች፣ ዕብራይስጡ የሚናገረው "ቤናይ ሃኤሎሂም" የቁም ትርጉሙም "የእግዚአብሔር ልጆች" ማለት ነው፡፡ በሌሎች ምንባቦች ግን ተመሳሳይ ቋንቋ እናገኛለን፡፡

የእስራኤልም መንግሥት ራሱ እንደ ዘፀአት ምዕራፍ 4 ቁጥር 22 እና ሆሴዕ ምዕራፍ 11 ቁጥር 1 በመሳሰሉ ክፍሎች ውስጥ የእግዚአብሔር ወንድ ልጅ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ እንደ 2ሳሙኤል ምዕራፍ 7 ቁጥር 14 እና መዝሙር 2 ቁጥር 7 ባሉት ክፍሎች ደግሞ የእስራኤል ሰብዓዊ ነገሥታትም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ የመጀመሪያው የሰው ዘር አዳምም፣ በሉቃስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 38 ላይ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተጠቅሷል፡፡

ሁላችንም ክርስቲያኖች እንደምናውቀው፣ በበርካታ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ አማኞች ልጆቹ ተብለው ተጠርተዋል፡፡ ይህንንም እንደ ማቴዎስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 9 እና 45፣ ሉቃስ ምዕራፍ 20 ቁጥር 36 እና ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 14 እና 19 በመሳሰሉ ክፍሎች ላይ እንመለከተዋለን፡፡ ጳውሎስም በገላትያ ምዕራፍ 3 ቁጥር 26 እንደጻፈው፡

> በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ (ሮሜ 3፥26)

ታዲያ "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው መጠሪያ በራሱ ለብቻው ኢየሱስ መለኮታዊ ነው የሚለውን ካላረጋገጠ፣ ቤተክርስቲያን ለምን ዋና ጉዳይ አድርጋ ያዘችው?

አዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ እንዴት እንደሚናገር ስንመለከት፣ የእግዚአብሔር ልጅነቱ ለየት ባለ መንገድ መሆኑ ግልጥ ይሆንልናል፡፡

> *በመሠረቱ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከምናገኛቸው ትኩረት ሳቢ ነገሮች ዋነኛው ኢየሱስ ልዩው የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ ያም እርሱ የእግዚአብሔር ማንነት ተካፋይ የመሆኑ ነገር ነው፡፡ ለየት ባለ መንገድ ስናስቀምጠውም ኢየሱስ ራሱ አምላክ ነው፡፡ እኛ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሆንነው በማደጎ (Adoption) በተገኘ ዝምድና ነው እንጂ በማንነት አይደለም። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ነው፡፡ እርሱ ለዘወትር የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ይኖራል፡፡ [ዶ/ር ቶም ሽሬነር]*

የኢየሱስ ልዩ ልጅነት በተለይም በዩሐንስ ወንጌል በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ለአብነት ያህል፣ በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እስከ 18፣ ኢየሱስ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ይነግረናል ፣ ማለትም እርሱ ራሱ እግዚአብሔርም አንድያ የአብ ልጅም ነው ማለት ነው፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 18 እስከ 23 ኢየሱስ እንደ አብ ልጅ፣ ከላይ የመጣ እንጂ ከዚህ ዓለም እንዳልሆነ ሲናገርም እንመለከተዋለን፡፡ ደግሞም በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 30 ላይ ኢየሱስ እርሱ እና አብ አንድ መሆናቸውን በተናገርበትም ክፍል ላይ እናገኘዋለን፡፡

ዮሐንስ ነገሩን ይበልጥ ግልጥ ያደረገበት ስፍራ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 18 ላይ ያለው ነው፡፡ በዚያ ስፍራ የጻፈውን አድምጡ፡

> ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ። እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ (ዮሐንስ 5፥18)

ኢየሱስ ስለ ራሱ  የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ ሲናገር፣ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ነኝ ማለቱ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሎ ሲናገር፣ እርሱ ልዩና መለኮታዊ ነው ማለቱ እንደሆነ ክርስቲያኖች የመረዳት መብት አላቸው፡፡

የኢየሱስ መለኮታዊ ልጅነት በተጨማሪም በሌሎች በርካታ የአዲስ ኪዳን ምንባቦችም ተገልጦ እናገኘዋለን፡፡ ይህንንም ጳውሎስ ከትስጉትነቱ በፊት እንኳን ኢየሱስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ ስለ መሆኑ ባስተማረበት በሮሜ ምዕራፍ 1 ቁጥር 3 እና 4 ደግሞም በምዕራፍ 8 ቁጥር 3 ላይ እናገኘዋለን፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ 3 እንደ እግዚአብሔር ልጅ፣ ኢየሱስ ፍጥረተ ዓለምን የፈጠረ የአብ አምሳል መሆኑ በተነገረበት ክፍልም እናገኘዋለን፡፡ በእነዚህና በሌሎችም ቦታዎች፣ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ የተገለጠው ዘላለማዊና መለኮታዊ ማንነቱን በሚገልፅ ለየት ባለ መንገድ ነው፡፡

ኢየሱስ መለኮታዊና ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለው አትኩሮት በትምህርተ ሥላሴ ውስጥ እንዲህ ተገልጧል፡

*እግዚአብሔር ሦስት ሰውነት፣ ግን አንድ ማንነት አለው፡፡*

አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ከስላሴ አንዱ የሆነው፣ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን ያስተምረናል፡፡ ግን ከእግዚአብሔርና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውስ ግንኙነት ምንድን ነው?

ቀደም ብለው በነበሩት ትምህርቶች እንደተነጋገርነው፣ በስላሴ ማንነት ላይ የተደረገው ጥናት የሚያተኩረው በእግዚአብሔር ማንነትና ጎላዊ ላይ ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ፣ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በኃይልም ቢሆን በክብር እኩል ነው፡፡ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት ወልድንም ጨምሮ የማይገደቡ፣ ዘላለማዊና የማይለዋወጡ ናቸው፡፡ ሦስቱም እንደ ጥበብ፣ ኃይል፣ ቅድስና፣ ፍትህ፣ መልካምነትና እውነት የመሳሰሉ ተመሳሳይ መሠረታዊ ባሕርያት አሏቸው፡፡

በንጽጽር ደግሞ፣ ስለ ስላሴ ያለው ኤኮኖሚያዊ አመለካከት የእግዚአብሔር አካላት አንዳቸው ከሌላቸው ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ይገልጥልናል፡፡ ከዚህም አመለካከት፣ እያንዳንዳቸው የተለያዩ ሃላፊነቶች፣ የተለያየ የሥልጣን እርከን እና እንዲያከናውኑ የተሰጣቸው ተግባር መኖሩን እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ፣ ክርስቶስ ዘወትር የእግዚአብሔር ልጅ፣ ለእግዚአብሔርም ሥልጣን ራሱን ያስገዛ ነው፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 38 ኢየሱስ ለአባቱ ያለውን መሰጠት ሲገልጥ የተናገረውን እናዳምጥ፡

*ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።* (ዮሐ 6፥38)

በዮሐንስ ምዕራፍ 8 ቁጥር 28 እና 29 ተመሳሳይ የሆነውን ነገር መግለጡን እነዚህን ቃላት ስናነብብ እንረዳለን፡

ስለዚህም ኢየሱስ፡- የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች

እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ።
የላከኝም ከእኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም አላቸው። (ዮሐ 8፥28-29)

በአዲስ ኪዳን ከዳር እስከዳር ወልድ ለአብ ሥልጣን ራሱን በፈቃዱ አስገዝቶ እናገኘዋለን፡፡ በመካከላቸው ግጭት የለም፣ ምክንያቱም ወልድና አብ ዘወትር ይስማማሉና፡፡ ነገር ግን ከፍ ያለው ሥልጣን የአብ ነው፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ በዚሁ የስላሴ ኤኮኖሚ ውስጥ፣ ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሥልጣን አለው፡፡ ለምሳሌ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 26 የተናገረውን አድምጡ፡

ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ (ዮሐ 15፥26)

በሎችም ምንባቦች፣ እንደ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 9 እና 1ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 11 ባሉት ክፍሎች፣ መንፈስ ቅዱስ "የክርስቶስ መንፈስ" ተብሎ ተጠርቷል እንደገናም መንፈሱ በክርስቶስ የተላከ መሆኑን አመልክቷል፡፡

እነዚህ ግንኙነቶች ወልድ የስላሴ ሁለተኛ አካል ነው በሚለው ድምዳሜ ተጠቃልለዋል፡፡ እርሱ የስላሴ ማንነት ሁለተኛ አካል ነው፣ ምክንያቱም ከአብ ወጥቶአልና እርሱም ሦስተኛውን አካል መንፈስ ቅዱስን ልኳል፡፡ በኤኮኖሚያዊ ስላሴ ወስጥ ሁለተኛው አካል ነው ምክንያቱም የመሃከለኛውን ስፍራ ይዟልና፡፡ እርሱ ለአብ የሚገዛ ሲሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን ሥልጣን አለው፡፡

በቀደመችው ቤተክርስቲያን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ለሙሉ መለኮት ነው የሚለው የእምነት አቋም በክርስትና እምነት ውስጥ ለድርድር የማይቀርብ ነው፡፡ በጥምቀታቸው ወቅት የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ በቃልኪዳን መልክ የሚናገሩ ሰዎች ከስላሴ ዝርዝር ሥራዎች ጋር የተያያዙ ስነ መለኮታዊ ጥቃቅን ነገሮችን ሁሉ ልቅም አድርገው እንዲያረጋግጡ አይጠበቅባቸውም፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አስመልክቶ ግን ያለማወላወል አቋማቸውን እንዲገልጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዛሬም ቢሆን፣ ኢየሱስ በእውነት ፍፁም አምላክ ነው ብሎ ማረጋገጥ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡

"የእግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ቃል ያለውን ወሳኝነት ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ "ጌታ" የሚለው ስያሜ እንዴት የኢየሱስን መለኮትነት እንደሚያመለክት እንመለከታለን፡፡

# ጌታ

አዲስ ኪዳን ኢየሱስን ጌታ ብሎ ሲጠራው፣ ኪዩሪየስ (Kurios) የተሰኘውን የግሪክ ቃል ፍቺ ይይዛል፡፡ ኪዩሪየስ (Kurios) ገዢ ወይንም ጌታ የሚለውን የተለመደ ቃል ፍቺ ይይዛል፣ ይህም የእንግሊዝኛው ቃል ጌታዬ (Sir) በማለት አገልግሎት ላይ የሚያውለውን የአክብሮት መጠሪያም ይዞ ያገለግላል፡፡ ለነገሩ፣ ኪዩሪየስ የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ጊዜ ለሰብዓዊ ሰዎችም አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይህንንም በማቴዎስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 24፣ ሉቃስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 36 እስከ 47፣ ኤፌሶን ምዕራፍ 6 ከቁጥር 5 እስከ 9 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናገኘዋለን፡፡

በተመሳሳይም፣ አዲስ ኪዳን ኪዩሪየስ የሚለውን ቃል የእግዚአብሔር ስም አድርጎም ተጠቅሞበታል፡፡ ይህንንም በማቴዎስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 25፣ ሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 16፣ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 39 እና በሌሎችም በርካታ ምንባቦች እናገኘዋለን፡፡ ይህንን ሰፊ አፈታት ከተመለከትን፣ በአዲስ ኪዳን ኪዩሪየስ የሚለው ቃል የኢየሱስን መለኮትነት ያመለክታል ብለን ለምን እናስባለን? ለምንድን ነው ቃሉ በምድር ያለውን ሥልጣንና ክብር ብቻ ለማመልከት የማንጠቀምበት? ብለን መጠየቅ መልካም ነው፡፡

*የክርስቲያኖች ኪዩሪየስ የሚለው ቃል አጠቃቀም ቁልፉ ብሉይ ኪዳን ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በዕብራይስጥ ነው፡፡ ሆኖም፣ ክርስቶስ ከመወለዱ ጥቂት ምዕተ-ዓመታት ቀደም ብሎ፣ የዕብራይስጡ ቅጂ ወደ ግሪክ ተተረጎመ፡፡ ይህም ትርጉም Septuagint ሰብዓ ሊቃናት በሚል መጠሪያ ይታወቃል፡፡ የአይሁድ ምሁራን ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ ሲተረጉሙ፣ ኪዩሪየስ የሚለውን የግሪክ ቃል 6700 ጊዜ ያህል እግዚአብሔር ለህዝቡ ራሱን የገለጠበትን ያህዌ (Yahweh) የተሰኘ ቅዱስ ስም ለመተርጎም ተጠቅመውበታል፡፡ ይህ የቀደምት ታሪክ ማስታወሻ አዲስ ኪዳን ለኢየሱስ ያዋለውን የኪዩሪየስ ፍቺ ለመረዳት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ምንም እንኳን ኪዩሪየስ የሚለው ቃል በራሱ የኢየሱስን መለኮትነት ባያስረዳም፣ የዚህ ቃል የብሉይ ኪዳን ቀደምት ታሪክ ማስታወሻ በበርካታ ምንባቦች ውስጥ የኢየሱስን መለኮትነት በግልጥ እንዲያመለክት አድርጎታል፡፡ (ዶ/ር ኬት ጆንሰን)*

*በአዲስ ኪዳን ከምናገኛቸው አስደናቂ ምንባቦች አንዱ*

*ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥
መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።”*

*(ፊልጵስዩስ 2፥10-11) በመሠረቱ፣ ጳውሎስ፣ በዚያን ወቅት የጠቀሰው ከኢሳያስ ነው፣ ያም ያህዌ ጌታ ነው ብሎ እያንዳንዱ ሰው የሚያውጅ መሆኑን የሚገልጥ ዝማሬ ነው፡፡ እርሱም ሆን ብሎ የብሉይ ኪዳኑን ምንባብ ወስዶ ያንኑ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ብሎ ተጠቅሞበታል፡፡ በዚያም ወቅት አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያው ምድራዊ ጌታ ብቻ ሳይሆን፣ ከእስራኤል ጌታ አምላክ ጋር አንድ እንደሆነ በግልጽ ያመለክት እንደነበር እውቅ ነበር፡፡ (ዶ/ር ፒተር ዎከር)*

እስኪ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 10 ቁጥር 9እና 13 ላይ የጻፈውን አድምጡ፡

> ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤… የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።

በቁጥር 13 ላይ ጳውሎስ የሚያጣቅሰው ከኢዩኤል ምዕራፍ 2 ቁጥር 32 ሲሆን ይህንንም የኢየሱስን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል የሚለውን ለማረጋገጥ ተጠቅሞበታል፡፡ ከኢዩኤል የተጠቀሰው ጥቅስ በብሉይ ኪዳን፣ ጌታ የሚለው ስም ያህዌ፣ አግባብነት ያለው የእግዚአብሔር ስም መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በቀላሉ ስናስቀምጠውም፣ ጳውሎስ ኢየሱስ ጌታ ነው ሲል፣ ኢየሱስ ያህዌ፣ የብሉይ ኪዳኑ ጌታና አምላክ ነው ማለቱ ነው፡፡

ኢየሱስን ከብሉይ ኪዳኑ አምላክ ጋር የሚያስተካክሉት የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ማቴዎስ ምዕራፍ 3፣ ማርቆስ ምዕራፍ 1፣ ሉቃስ ምዕራፍ 3 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ሲሆኑ በዚያም ኢየሱስ በኢሳያስ ምዕራፍ 40 የተጠቀሰውና መጥምቁ ዮሐንስም መንገዱን የጠረገለት ጌታ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ተመሳሳዩን መግለጫ በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 10 ላይ ጌታ ኢየሱስ በመዝሙር 102 ከቁጥር 24 -25 ዓለምን የፈጠረ ተብሎ የተጠቀሰው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዝርዝሩ እንዲህ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡

እንግዲህ፣ በአዲስ ኪዳን ሰዎች ኢየሱስን “ጌታ” ሲሉት ዘወትር መለኮትንቱን ማመልከታቸው ነው እያልን አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰብዓዊ ከበሬታን ሊሰጡትም ሲሹ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ልክ እኛ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እንደምናደርገው ስታውጅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ፣ በአምላክነቱም የስላሴ ምሉዕ አባል፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ እኩል መለኮታዊ የባህርይ መገለጫዎች ያሉት ነው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ማረጋገጣችን ነው፡፡

የክርስቶስ መለኮትነት ለክርስትና ሕይወት ሁሉን ዓይነት እንድምታ አካትቷል፡፡ ለምሳሌ፣ በጸሎቶቻችንና በዝማሬዎቻችን ሁሉ ኢየሱስን እንደ አምላክ ልናመልከውና እውቅና ልንሰጥ

ይገባናል ማለት ነው፡፡ ልክ ወደ አብና ወደ መንፈስ ቅዱስ እንደምጸልይ ሁሉ ወደ እርሱም እንጸልያለን ማለት ነው፡፡ እናም እግዚአብሔር ራሱ ከኀጢአት እንደዋጀን በማወቅ ከድነት ዋስትናችን አንፃር ትልቅ መጽናናትንና እርግጠኝነትን እንይዛለን ማለት ነው፡፡ እነዚህና ሌሎችም በክርስትና ሕይወት ውስጥ የሚገኙ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የሚያርፉት በክርስቶስ መለኮትነት ባለን እምነት ላይ ነው፡፡

ይህንን የኢየሱስን መለኮትነት በልቡናችን ይዘን፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የእርሱ ሰውነት የተንፀባረቀበትን መንገድ ወደ መመልከቱ እንሻገራለን፡፡

# 3. ሰውነት

ባለፉት በርካታ ምዕተ-ዓመታት ውስጥ፣ ብዙ የነገረ-መለኮት ምሁራን ኢየሱስ ሰው መሆኑን ተቀብለዋል፣ መለኮትነቱን ግን ከጥያቄ ውስጥ አስገብተውታል፡፡ በቤተክርስቲያን ቀደምት ዓመታት ግን፣ ኢየሱስን ሰውነት ሰዎች ጥያቄ ውስጥ የማስገባታቸው ነገር የተለመደ ነበር፡፡ በዘመኑ የነበሩ እውቅ ፍልስፍናዎች ሰዎች አምላክ ራሱን እንደሰው ለማዋረድ ፈቀደ የሚለውን በአንፃራዊነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ቀለል አድርገውት ነበር፡፡

አምላክ በእውነት ሰው ሆኗል የሚለውን ሃሳብ መቀበል ግን ከብዷቸዋል፡፡ ሰዎች አካላዊና ስሜታዊ ናቸው፡፡ በእነርሱ ግምትም፣ እግዚአብሔር ክብሩንና ማንነቱን የተዋረደውን፣ ተፈጥሯዊውን የሰው ፍጥረት ለመውሰድ ያመቻምቻል ብለው ማመን ቸግሯቸዋል፡፡ በሚያሳዝንም መንገድ፣ በርካታ ዘመናዊ ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር ወልድ ሁሉን ደካማነቱንና ውሱንነቱን የያዘ ፍፁም ሰው ሆኖ ወደ ምድር መጣ የሚለውን ነገር ማመን ይቸግራቸዋል፡፡

ኢየሱስ ፍፁም ሰው መሆኑን ለመግለጥ፣ ስለ እርሱ ሰውነት ሦስት ሰፊ ገፅታዎች እንነጋገራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ እርሱ ሰብዓዊ ልምምድ እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ እርሱ ሰብዓዊ ቢሮ እንወያያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ስለ ሰብዓዊ ተፈጥሮውና ከመለኮታዊ ማንነቱ ጋር ስላው ግንኙነት ጥቂት እንነጋገራለን፡፡ እስኪ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ከተዘረዘረው ሰብዓዊ ልምምዱ እንጀምር፡፡

## ልምምድ

የኢየሱስ በርካታ ልምምዶች እርሱ እውነተኛ ሰው መሆኑን ያረጋግጣሉ ምክንያቱም እነዚያን የመሰሉ ልምምዶች ያሉት ሰው ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ከሃይማኖት መግለጫው የተወሰደውን እስኪ እናድምጥ፡

*[ኢየሱስ] ከመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣*

*ከድንግል ማርያም በተወለደ፣*

*በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣*

*በተሰቀለ፣ በሞተ እና በተቀበረ፤*

*ወደ ሲዖልም በወረደ፡፡*

*በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፡፡*

እነዚህ ልምምዶች ቢያንስ አራት የኢየሱስን ሰውነት ገፅታዎች ያረጋግጡልናል፡፡ እነርሱም፣ ትውልዱ፣ አካሉ፣ ነፍሱ እና ትንሣኤው ናቸው፡፡ በመጀመሪያም መፀነሱንና ልደቱን ያካተተውን ትውልዱን በመመልከት እንጀምራለን፡፡

# ትውልድ

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ስለ ኢየሱስ ትውልድ የሚናገረው በእነዚህ ቃላት ነው፡

*[እርሱ] ከመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣*

*ከድንግል ማርያም በተወለደ፡፡*

ከኢየሱስ መፀነስና መወለድ ጋር በተያያዘ እጅግ እንግዳ የሆኑ ዝርዝሮች እንዳሉ ሁላችንም እንቀበላለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የተፀነሰው ከሰብዓዊ አባት ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ከዚያም ባሻገር የእናቱ ድንግልናም ሳይነካ ነው የተፀነሰው፡፡ እነዚህን ዝርዝሮች ሰፋ አድርገን በዚሁ ትምህርት ወደፊት እናያቸዋለን፡፡ ለአሁኑ ግን፣ በመሠረታዊ ደረጃ የሰብዓዊ ልምምድ መገለጫ በሆኑ ሃሳቦች ላይ እናተኩራለን፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ኢየሱስን “የተፀነሰ” ብሎ ሲናገር፣ ከአዳምና ከሄዋን ኋላ የመጣው የሰው ዘር በሙሉ በመጣበት መንገድ ኢየሱስም እንደመጣ የሚገልጥ ሃሳብ የያዘ

ነው፡፡ ማለትም በእናቱ ማኅፀን እንዳለ ትንሽ ሕፃን ማለት ነው፡፡ ማቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 18፤ ሉቃስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5 እና 6፤ ገላትያ ምዕራፍ 4 ቁጥር 4 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ቁጥር 5 የመሳሰሉ ምንባቦች እግዚአብሔር ኢየሱስን በማርያም ማኅፀን ውስጥ ያበጀው ልክ የሰውን ዝርያ በሚያበጅበት መንገድ መሆኑን ያመለክቱናል፡፡

ሉቃስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 34 እስከ 37 የማርያምን መፀነስ አስመልክቶ በማርያምና በመልአኩ በገብርኤል መካከል የተደረገውን ንግግር ያስነብበናል፡፡

> ማርያምም መልአኩን። ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።
> መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።
> እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤
> ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። (ሉቃስ 1፥34-37)

ማርያም እየሰማችው ባለው መንገድ ልጅን ለመፀነስ ተዓምር እንደሚያስፈልግ ተረድታለች፡፡ በእርሷም ሕይወት የተፈፀመው ይኸው ተዓምር ነው፡፡

> *የኢየሱስ ተዓምራዊ ፅንሰት እርሱ ፍፁም መለኮትና ፍፁም ሰው መሆኑን አረጋግጧል፣ ይህ ማለት ግን ፍፁም ሰው ከመሆን ያሳንሰዋል ማለት አይደለም፡፡ አፀናነሱ ተዓምራዊ መሆኑ እርግጥ ነው፣ እንዲያውም በቤዝዎታዊ ታሪኮች ከተከናወኑ ታላላቅ ተዓምራት አንዱ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን፣ የኢየሱስን ፅንሰት፣ በማኅፀን ውስጥ ከነበረው አካላዊ አወቃቀርና እድገት አንፃር ስንመለከተው ልክ እንደ ሌሎች ሰብዓዊ ዝርያዎች ዓይነት ነበር፡፡ እርሱ ያለፈው፣ ልክ መደበኛው የሰው አወላለድ ሂደት ይጓዝ በነበረበት መስመር ነበር፡፡ ለእድገቱ የሚጠቀመውን ጡት መጥባቱና ለምግቡም የእናቱ ጥገኛ የመሆኑ ነገር፣ አፍንጫው በንፍጥ መዝረክረኩና የሽንት ጨርቅ እየተቀየረለት የማደጉ ሰብዓዊ ሒደትም እንደዚሁ ለእርሱም የተጠበቀ ነበር፡፡ ከተራ ሰብዓዊ ሰውነት የዘለለ ነገር ቢኖረውም፣ ፍፁም ሰውነቱ ግን አይቀነስም፡፡ [ዶ/ር ሮበርት ጂ. ሊስተር]*

አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ ሰብዓዊ አባት ስለሌለው ፍፁም ሰው ሊሆን አይችልም የሚል ሙግት ይነሳል፡፡ ግን ልብ ልንለው የሚገባ ነገር የመጀመሪያዎቹም ሰዎች እኮ ሰብዓዊ አባት

ያልነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እንደሚነግረን፣ አዳም የተበጀው ከምድር አፈር ሲሆን ሄዋን ደግሞ ከአዳም የጎን አጥንት ነበር የተሠራችው፡፡ ማናቸውም ወላጅ አልነበራቸውም፡፡ አንዳቸውም ከሴት አልተወለዱም፡፡ ሁለቱም ግን ሙሉ በሙሉ እና እውነተኛ ሰዎች ነበሩ፡፡ ምንም አንኳን አፀናነሱ ከተለመደው መንገድ ወጣ ያለ ቢሆንም፣ ኢየሱስም እንዲሁ ፍፁም ሰው ነው፡፡

ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንረዳው፣ የኢየሱስ በማርያም ማኅፀን ውስጥ የማደጉ ነገር በመወለዱ ወደ ሙላት እንደመጣው ፍፁም ተፈጥሮአዊ ሁነት ነበር፡፡ በምትሃታዊ መንገድ አልተከሰተም፣ ወይንም በተወለደበት ሰዓት ከሰማያት አልወረደም፡፡ ማቴዎስ ምዕራፍ 1 እና ሉቃስ ምዕራፍ 2 እንደሚገልፁልን የማርያም መፀነስ አስቀድሞ ተሸሽጎ የቆየ ቢሆንም፣ በኋላ ግን ግልፅ ሆኗል፡፡ እጮኛዋ ዮሴፍ እንኳን እግዚአብሔር በህልም እውነቱን እስኪነግረው ድረስ፣ ታማኝነቷን እንዲጠራጠር አድርጎታል፡፡ የመጨረሻ ውጤቱም ኢየሱስ እውነተኛ ሰብዓዊ ህፃን ሆኖ ተወልዷል፡፡

> *ኢየሱስ ፍፁም እና ይህ ቀረው የማይባል ሰው ነው፡፡ የክርስቶስ ተዓምራዊ መፀነስ በምንም መንገድ እውነተኛ ሰውነቱን አይቀንሰውም፡፡ እንዲያውም ኢየሱስ በተዓምራዊ ፅንሰቱ የሰው ዘር ሊሆን የሚገባውን ማንነቱን አሳይቶናል ምክንያቱም በክርስቶስ ውስጥ ከኃጢአት ነፃ የሆነ ሰው መሆን መቻሉን አይተናል፣ በመንግሥተ-ሰማያትም የምንሆነው እንደዚያ ነው፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ኬ. ቶኔስ]*

የኢየሱስን ትውልድ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ አካሉ ሰብዓዊነቱን እንዴት እንዳረጋገጠ እንመለከታለን፡፡

# አካል

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የሚያረጋግጠውን በአዕምሯችን ውስጥ አድርገን እንነሳለን፡

> *[ኢየሱስ] በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መከራን የተቀበለ፣*
>
> *የተሰቀለ፣ የሞተ እና የተቀበረ፡፡*

በነዚህ ቃላት፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ለኢየሱስ የሰጠው የባህርይ መገለጫ እውን ሊሆን የሚችለው እውነተኛ ሰብዓዊ አካላዊ ማንነት ካለው ብቻ እንደሆነ አመልክቷል፡፡

በማቴዎስ ምእራፍ 27፣ ማርቆስ ምእራፍ 15፣ ሉቃስ ምዕራፍ 23 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 18 እና 19 እንደተጠቀሰው የኢየሱስን መያዝና መሰቀልን ስንመለከት፣ ኢየሱስ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን በተለያየ መንገድ መከራን ተቀብሏል፡፡ ተገርፏል፣ የእሾህ አክሊል እንዲደፋ ተገድዷል፣

ተተፍቶበታል፣ አላግጠውበታል፣ እናቱን በዱላ ተመትቷል እስከተሰቀለበት ስፍራ አጋማሽ ድረስ መስቀሉን ተሸክሞ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡

የኢየሱስ መከራ፣ ስቅለት፣ ሞት እና መቀበር እርሱ የሚመታ፣ የሚደማ፣ በወታደሮች አንግልት የሚደርስበት፣ በድካም ምክንያት የሚዝለፈለፍ፣ የሚገደል እና ነፍሱም ስትለየው በመቃብር ውስጥ የሚቀበር ሰብዓዊ አካል ያለው ሰው መሆኑን ይገልጣሉ፡፡

ሰብዓዊ አካል የመኖሩ ነገር ግድ ነው ምክንያቱም የሰውን ዘር ኃጢአት ለማስተሰረይ መለኮታዊ ፍርድ የሚፈፀምበት እውነተኛ ሰብዓዊ ሰውነት ይኖር ዘንድ የእግዚአብሔር ፍትህ ግድ ይላል፡፡ ይህንንም አትኩሮት በሮሜ ምዕራፍ 7 ቁጥር 4፣ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 21 እና 22 እና በዕብራውያን ምእራፍ 10 ቁጥር 10 ላይ እናገኘዋለን፡፡

አንድ ምሳሌ ለመውሰድ ያህል፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 14 እስከ 17 የተጻፈውን አድምጡ፡

> እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥... የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥...በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው። (ዕብ 2፥14-17)

ይህ ምንባብ በግልፅ እንዳስቀመጠው፣ የእኛን ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ፣ ኢየሱስ በስጋና በደም ይካፈልና ሰብዓዊ አካል ይኖረው ዘንድ ግድ ነበር፡፡

ይህንን የኢየሱስን ትውልድና አካል መረዳት በልቡናችን ይዘን፣ የኢየሱስ ነፍስ ሰብዓዊ ተፈጥሮውን ወደ ምልአት ያመጣ መሆኑን እንመልከት፡፡

# ነፍስ

ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ዘር የማትሞተው ነፍስ ማደሪያ የሆነ የሚሞት አካል እንዳለው ደጋግመው ይነግሩናል፡፡ ስለ ነፍሳችንም በርካታ መግለጫዎችን ይጠቀማል፣ የተለመዱትም "ነፍስ"ና "መንፈስ" ናቸው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 12 እና 1ተሰሎንቄ ምዕራፍ 5 ቁጥር 23 መሠረት በማድረግ አንዳንድ ትውፊቶች "ነፍስ"ና "መንፈስ" የእኛነታችንን የተለያዩ ክፍሎች ናቸው ይላሉ፡፡ ነገር ግን በግምት ወደ 200 የሚጠጉ ጥቅሶች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ውስጣዊ ማንነታችንን አካላዊ ያልሆነውን ማንነታችንን በጠቅላላ ለመግለጥ ሁለቱ ቃላት በተለዋዋጭነት እንደገቡ ይነግሩናል፡፡ እንግዲያው፣ "ነፍስ"ና "መንፈስ" የሰውን አንድ ማንነት የሚያንጸባርቁና ሰውም አካልና ነፍስ አለው የሚለውን ድምዳሜ መያዝ የተመረጠ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡

በሉቃስ ምዕራፍ 23 ቁጥር 46፣ ሲሞት ስለ "ነፍሱ" ወይም "መንፈሱ" ተናግሯል፡፡ በዚያ የተናገረውን አድምጡ፡

> ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ። (ሉቃስ 23፥46)

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት፣ ሰውነቱ ወደ መቃብር ሲገባ፣ ሰብዓዊ መንፈሱ ወይንም ነፍሱ በእግዚአብሔር አብ እጅ ውስጥ እንደምትሆን አመልክቷል፡፡

እንደ መንፈሳዊ ማንነታችን መገለጫ፣ ነፍሳችን የኅሊናችን መኖሪያ ናት፡፡ ሰውነታችን ሲሞት፣ ነፍሳችን ከሥጋችን ተለይታ ግን በንቃተ ኅሊናዋ ትቀጥላለች፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫውም ኢየሱስ በሞተ ወቅት ተመሳሳይ ነገር እንደሆነ ያብራራል፡፡ ይህንንም እንዲህ ሲል ይገልጠዋል፡

> *ወደ ሲዖልም በወረደ፡፡*

በዚህ ስፍራ፣ የሃይማኖት መግለጫው የሚገልጠው ኢየሱስ ሲሞት፣ ኅሊናው፣ ነፍሱ ከሥጋው መለየቷን ነው፡፡ ሥጋው በመቃብር በቆየባቸው ቀናት፣ ነፍሱ ወደ ሲዖል ወርዳ ነበር፡፡ በዚህ ትምህርታችን ወደ ኋላ ላይ የዚህን መስመር ፍቺ በበለጠ ጥልቀት እንመለከተዋለን፡፡ ለአሁኑ ግን፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የኢየሱስ ወደ ሲዖል መውረድ ኢየሱስ የሰው ነፍስ የነበረው መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ማመልከት ብቻ እንሻለን፡፡

በመጨረሻም፣ የኢየሱስን ሰብዓዊነት የትውልዱን፣ የአካሉን እና የነፍሱን ማስረጃዎች በመጠቀም ለማረጋገጥ ከመሞከራችን ባሻገር፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የኢየሱስን ትንሣኤ ነፍሱ ከሥጋው ጋር እንደገና የተዋሃደበች መሆኑን በማመልከት የሚናገረውን እንመለከታለን፡፡

# ትንሣኤ

ትንሣኤ ኢየሱስ እውነተኛ ሰው መሆኑን አረጋግጧል ምክንያቱም የእርሱ ምሉዕና የከበረ ስብዕናው ሥጋውና ነፍሱ በአንድነት መልሰው የተዋሃዱበት መሆኑን አሳይቷል፡፡ የሥጋ ትንሣኤው የተገለጠው ሰብዓዊ ነፍሱ ከከበረው አካሉ ጋር ሲገናኝ ነው፡፡ አዎን፣ የትንሣኤ አካሉ ከዚያን በኋላ ሞት ላይይዘው ከብሯልና በተወሰነ መልኩ የተለየ ነበር፡፡ ነገር ግን በምንም መንገድ ያነሰ አካል ወይንም ሰውነት ነበረው ማለት አይደለም፡፡ በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 በጠቅላላው ስንመለከት፣ የኢየሱስ የትንሣኤ አካል አማኞች ወደ ፊት የሚለብሱት

የትንሣኤ አካል በኩራት ሆኖ ተገልጧል፡፡ እንዲያውም፣ ሰብዓዊ ሰውነታችን ወደፊት ምን እንደሚመስልም ያመለክተናል፡፡

ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 15 ከቁጥር 20 እስከ 23 የጻፈውን አድምጡ፡

> አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።
> ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና።
> ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።
> ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፥
> በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው፤ (1ቆሮ 15፥20-23)

ልክ አዳም የመጀመሪያው የሰው ዘር ሆኖ እንደተፈጠረ ሁሉ፣ ኢየሱስም በክብር የተነሣው የመጀመሪያው የሰው ዘር ሆኗል፡፡ ከእርሱ በፊት የነበሩት ሁሉ ሕያዋን ይሆናሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በኢየሱስ በራሱ ይነሣሉ፡፡ ሄኖክና ኤልያስም ሞትን ሳያዩ ወደ ሰማይ ተወስደዋል፡፡ ሆኖም ከእነርሱ አንዳቸውም የከበረና የማይሞት አካል አልለበሱም፡፡

የኢየሱስ አካል የከበረ ቢሆንም እንኳን፣ አሁንም ፍፁም ሰውነቱን እንደያዘ ይዘልቃል፡፡ ይህም ማለት ልክ እግዚአብሔር በዚያ ታላቅ የሙታን ትንሣኤ እግዚአብሔር አካላችንን ሲያድስ ምሉዕ ሰውነታችን የተጠበቀ እንደሚሆነው ዓይነት ማለት ነው፡፡

> *እርሱ ጨቅላ ሕፃን ነበር፡፡ በሕፃንነቱም ወራት በእናቱ ሙሉ በሙሉ የሚደገፍ ነበር፡፡ ሉቃስ እንደሚነግረንም እርሱ ፣ በቁመትና በሞገስ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር፡፡ ልክ እኛ እንደምንራብ ተርቧል፣ እንደምንጠማ ተጠምቷል፣ በቀራኒዮ መስቀልም ላይ እኛ የሰው ልጆች እንደምንሞት ሞቶ ነበር፡፡ እርሱ ፍፁም ሰው ብቻ ሳይሆን፣ ፍፁም አምላክም ነው፣ እውነቱ ግን ኢየሱስ የተረጋገጠ የሰው ዘር ብቻ ሳይሆን፤ እንከን የለሹም ሰው ነው፡፡ [ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር፣ ትንሹ]*

የኢየሱስን ሰውነት ከልምምዱ አንፃር ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ትኩረታችንን በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ክርስቶስ ተብሎ ወደ ተገለጠው ሰብዓዊ ቢሮው እናደርጋለን፡፡

# ቢሮ

የኢየሱስ አገልግሎት በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው በእነዚህ ቃላት ተገልጧል፡

*በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፡፡*

በዘመነኛው ክርስትና፣ ብዙ አማኞች “ክርስቶስ” የሚለው ቃል የክርስቶስ ስያሜ አካል ከመሆን ይልቅ የኢየሱስ አገልግሎት መጠሪያ መሆኑን አያውቁም፡፡ በዚህ ረገድ፣ “ክርስቶስ” የሚለው ቃል “ንጉሥ” ወይም “መስፍን” ከመሳሰሉት ቃላት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ስለ ኢየሱስ ሰብዓዊ ቢሮ በሁለት ክፍሎች እንነጋገራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ “ክርስቶስ” በመባል ስለሚታወቀው ቢሮ ብሉይ ኪዳናዊ ዳራውን እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ የዚህ ቢሮ ምልዐት በኢየሱስ መገለጡ የጌታችንን ሰውነት እንደሚያመለክት እናብራራለን፡፡ በመጀመሪያ “ክርስቶስ” የተባለውን ቢሮ ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እንዳስሳለን፡፡

# ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ

የእንግሊዝኛው “Christ” የሚለው ቃል በግሪኩ Christos የተሰኘው ቃል ፍቺ ሲሆን፣ የብሉይ ኪዳኑ የዕብራይስጡ mashiachor ወይን “messiah” የሚለው ቃል ፍቺ ማለትም “የተቀባው” የሚለውን ትርጓሜ የሚይዝ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን “የተቀባው” የሚለው ቃል፣ ለየት ባለ መንገድ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ እግዚአብሔር ለሾማቸው ሁሉ ጥቅም ላይ የሚውል ሰፊ አባባል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ1ዜና ምዕራፍ 16 ቁጥር 22 ነቢያት የተቀቡ ተብለዋል፡፡ ዘሌዋውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 3፣ 5 እና 16 ደግሞ ስለተቀቡት ካህናት ይናገራል፡፡ በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 26 ቁጥር 9፣11 እና 16 ላይ ዳዊት ሳዖልን የእስራኤል ንጉሥ በመሆኑ የተቀባ ይለዋል፡፡

ዘሌዋውያን ምዕራፍ 21 ከቁር 10 እስከ 12 የሊቀ ካህኑን መቀባት እንዴት እንደሚገልጠው አድምጡ፡

> በራሱም ላይ የቅባት ዘይት የፈሰሰበት፣ የክህነትም ልብስ ይለብስ ዘንድ የተቀደሰ ከወንድሞቹም የበለጠው ካህን ራሱን አይግለጥ ልብሱንም አይቅደድ፡፡ ወደ በድንም ሁሉ አይግባ በአባቱም ወይም በእናቱ አይርከስ፡፡ የአምላኩም ቅባት ዘይት ቅዱስነት በላዩ ነውና ከመቅደስ አይውጣ፣ የአምላኩንም መቅደስ አያርክስ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ (ዘሌ 21፥10-12)

በዚህ ስፍራ እንደምንመለከተው፣ የቅብዓቱ ሥነ-ሥርዓት ሰዎችን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይለያቸዋል፡፡

በብሉይ ኪዳን “የተቀባ” የሚለው ቃል አገልግሎት ላይ ከዋለባቸው ጠቀሜታዎች ዋነኛው በእስራኤልና በይሁዳ ላይ በንጉሥነት ለሚያገለግሉት የዳዊት ዝርያዎች ጥቅም ላይ የዋለበት

መንገድ ነው፡፡ ይህንንም እንደ:- መዝሙር 89 ቁጥር 38 እና 51፣ መዝሙር 132 ቁጥር 10 እና 17 እና 2ዜና ምእራፍ 6 ቁጥር 42 ላይ እናገኘዋለን፡፡ በዳዊት የሕይወት ዘመን፣ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚፀና ሥርወ-መንግሥት ከልጆቹ በአንዱ እንደሚሰጠው ተስፋ በመስጠት ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳንን አደረገ፡፡ መዝሙር 89 ቁጥር 3 እና 4 እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በዚህ መንገድ ያስቀምጠዋል፡

> ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፣ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ፡፡ ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፣ ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ፡፡ (መዝሙር 89፥3-4)

እንግዲህ፣ ታዲያ የዳዊት ልጆች እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶላቸው ሳለ ለምን በስተመጨረሻው ዙፋናቸውን አጡ የሚል ግርታ ቢፈጠር አይገርምም፡፡ መልሱ ግን በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ የተካተቱት በረከቶች ተፈፃሚነት የዳዊትን ዝርያዎች መታዘዝ በሚሻ መልክ ነው የተቀመጠው የሚለው ነው፡፡ ይህም ቅድመ ሁኔታ በ2ዜና ምዕራፍ 6 ቁጥር 16፣ በመዝሙር 89 ከቁር 30 እስከ 32 እና በመዝሙር 132 ቁጥር 12 ላይ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ስለዚህም፣ የዳዊት ዝርያዎች በእግዚአብሔር ላይ ሲያምፁ፣ ዙፋናቸውን ያጣሉ፡፡

ለአብነት ያህል፣ በ922 ዓ.ዓ፣ በዳዊት የልጅ ልጅ በሮብዓም ዘመን፣ ዐሥሩ ነገዶች ከዳዊት ሥርወ-መንግሥት ተቆርጠው ለኢዮርብዓም ተሰጥተው ነበር፡፡ ስለዚህ ሁነት በ1ዜና ምዕራፍ 11 እና 12 ላይም እናነብባለን፡፡ ኢዮርብዓምን የተከተሉት ነገዶች የእስራኤል መንግሥት ተብለው ሲጠሩ፣ ሮብዓምን የተከተሉት ቅሬታዎች ደግሞ የይሁዳ መንግሥት ተብለው ተጠሩ፡፡

በኋላም፣ በ587 ዓ.ዓ. ፣ ከዝርያዎቹ አንዱ የሆነው ኢኮንያ ከመንግሥቱ ሲነቀልና መንግሥቱም ለባቢሎናውያን አልፎ ሲሰጥ የይሁዳም መንግሥት ከዳዊት ቤት ላይ ተወሰደ፡፡

በዚሁ ዘመን አካባቢ፣ በርካታ ነቢያት እግዚአብሔር ታላቁን “መሲህ” ወይንም “የተቀባውን” እንደሚልክ ትንቢት ይናገሩ ነበር፡፡ እርሱም ከዳዊት ዘር የሆነ ታላቅ ንጉሥ፣ የእስራኤልንና የይሁዳንም መንግሥታት አንድ የሚያደርግ እንደሆነ ይናገሩ ነበር፡፡

> *በብሉይ ኪዳን፣ መሲህ በመባል የሚጠራው ገፀ ባህርይ የሚታወቀው በንጉሥነት ነው፡፡ ያም ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ ነው፡፡ ዳዊት ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተቀብሏል፣ ይህም ቃል ኪዳን አንድ ቀን ከእርሱ ጋር ለየት ያለ “የእግዚአብሔር ልጅነት” ግንኙነት ባለው እርሱ በሚያስነሳው ንጉሥ ተፈጻሚ እንደሚሆንና ይህም ንጉሥ እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ መንግሥቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ለዘላለም እንደሚፀና፣ ፍትህንና ጽድቅንም እንደሚመሠርት ተስፋ የተገባበት ነበር፡፡ እንግዲያው፣ የብሉይ ኪዳኑን መሲህ ስናነሳ ስለ*

*ንጉሡ መናገራችን ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ንጉሥ ወደር የለሽ፣ የእግዚአብሔርን ማዳንና ነፃ አውጪነት ወደ ምድር የሚያመጣ ንጉሥ ነው፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ]*

በርካታ የብሉይ ኪዳን ነቢያት መሲሁ ወይንም ክርስቶስ ከዳዊት ዘር እንደሆነ፣ ምርኮኞችንም ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንደሚመልስና ለታደሰችውም ምድር የእግዚአብሔርን ታላቅ በረከት እንደሚያመጣ ተናግረዋል፡፡ ለምሳሌ፣ እነዚህን መሳይ ትንቢቶች በኤርምያስ ምዕራፍ 23 ከቁጥር 5 እስከ 8፣ ምዕራፍ 30 ቁጥር 8 እና 9 እና ምዕራፍ 33 ከቁጥር 14 እስከ 17 ላይ እናገኛቸዋለን፡፡ እንደገናም፣ በሕዝቅኤል ምዕራፍ 34 ከቁጥር 20 እስከ 31 እና ምዕራፍ 37 ከቁጥር 21 እስከ 28 ላይም እናገኛቸዋለን፡፡ ደግሞም በዘካርያስ ምዕራፍ 12 እና 13 ላይም ይገኛሉ፡፡ አንዱን ለአብነት ብንወስድ፣ እስኪ በኤርምያስ ምዕራፍ 23 ከቁጥር 5 እስከ 6 ያለውን አድምጡ፡

> እነሆ፥ ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል
> እግዚአብሔር፥ እርሱም እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥ ይከናወንለታልም፥
> በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል።
> በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፥
> የሚጠራበትም ስም። እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።
> (ኤር 23፥5-6)

እነዚህን በመሳሰሉ ትንቢቶች፣ ብሉይ ኪዳን ከዳዊት ዘር የሆነውንና ከመከራቸውና ከስቃያቸው በማዳን ወደ እግዚአብሔር የከበረ በረከት የሚያመጣቸውን መሲሁን እንዲጠባበቁ የእግዚአብሔርን ህዝብ ያበረታታ ነበር፡፡

ይህንን በብሉይ ኪዳን የተቀመጠ የመሲህነት አገልግሎት ዳራ ከተመለከትን፣ የዚህ አገልግሎት ቢሮ ምልዓት እንዴት ወደ እርሱ ስብዕና እንደሚያመለክት እንዳስሳለን፡፡

# ምልዓት በኢየሱስ

አዲስ ኪዳን ኢየሱስን በክርስቶስነቱ ከ500 ቦታዎች በላይ ጠቅሶታል፡፡ ይህም በአብዛኛው የተጠቀሰው ስለ ክርስቲያናዊው አተያይ ምንም ሳይል፣ ብሉይ ኪዳን የጠቀሰው ታላቁ መሲህ መሆኑን በሚያመለክት መንገድ ነው፡፡ የትኞቹንም ጥርጣሬዎች ለማስወገድ ሲባል ግን፣ በዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ “መሲህ” ተብሎ የተጠራባቸው ና ዮሐንስ “መሲህ” ማለት “ክርስቶስ” ማለት መሆኑን ያብራራባቸው ሁለት ምንባቦች አሉ፡፡ እነዚህም፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁር 41 እና ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 25 እና 26 ናቸው፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ አንዱን እንመልከት፡፡

ኢየሱስ በምንጩ አጠገብ ካገኛት ሴት ጋር ያደረገውን ንግግር አስኪ እናዳምጥ፡

> ሴቲቱ። ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።
>
> ኢየሱስ፡- የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት። (ዮሐ 4፥25-26)

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተነገረለት መሲህ መሆኑን አስረግጦ ተናግሯል፡፡ ዮሐንስም “መሲህ” የሚለው ቃል በግሪኩ ክርስቶስ የተባለው ፍቺ መሆኑን በማመልከት አብራርቶ አስቀምጦታል፡፡ ይህም ለእኛ የሚያስተላልፈው መልዕክት በየትኛውም ኢየሱስ በ“ክርስቶስነት” ተገልጦ ካገኘነው፣ በብሉይ ኪዳን የተነገረለት መሲህ መሆኑን ልንረዳ እንደሚገባ ነው፡፡

ግን የኢየሱስ  የመሲህነት ወይንም የክርስቶስነት አገልግሎቱ እንዴት አድርጎ ነው ስብዕናውን የሚያረጋግጠው? እግዚአብሔር በቀላሉ በመለኮታዊ ክብሩ ወደ ምድር በመምጣት ለምን ሕዝቡን አላዳነም? ወይንስ አንድ መልአክ ልኮ በእርሱ ፊት ሞገስ ያገኘችውን ሀገር እንዲመራ ያላደረገው ለምንድን ነው?

በብሉይ ከዳን ትንቢቶች መሠረት፣ መሲሁ ሰው ሊሆን ይገባዋል ምክንያቱም የዳዊት ልጅ ነውና፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሁሉ፣ ከእርሱ ወገን አንዱ እስራኤልን ለዘላለም እንደሚገዛ እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር፡፡ በመሠረቱም፣ የዳዊት ዝርያዎች ሁሉ ሰዎች ነበሩ፡፡

> *እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች ጋር በቃል ኪዳን ዝምድናን ይመሠርታል፡፡ ይህንን በፈቃዱ ያደርገዋል፡፡ ይህንን እንዲያደርግ የሚያስገድደው የለም፡፡ ምንጩ ራሱ ነው፡፡ በአንድያ ልጁ መካከለኝነት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን መግባቱ ሉዓላዊ ምርጫው ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ቃል ኪዳን ከገባ፣ ቃል ኪዳኑ የበረከትም ይሁን የመርገም የቃል ኪዳኑን አንቀፆች ሁሉ የመፈፀም ግዴታ ውስጥ ይገባል፡፡ ያንን ቃል ኪዳን የማፍረስ ነፃነት የለውም፡፡  [ዶ/ር ዴሪክ ደብሊዩ ኤች ቶማስ]*

> *ምንም እንኳን ነገሩ የሚያስገርም ቢመስልም፣ እግዚአብሔር በገባው ቃል መሠረት ራሱን ግዴታ ውስጥ አስገባ፡፡ ቃል ኪዳን በሚገባበት በየትኛውም ዘመን ሁሉ፣ በውስጡ የተቀመጡትን አንቀፆች ለመጠበቅ ራሱን ይሰጣል፡፡ ለቃል ኪዳን ሕዝቡ ያለውን ዘላላማዊ ፍቃዱን ለመፈፀም ያስቻለው ዘንድ ራሱን በዚህ መንገድ ግዴታ ውስጥ ማስገባትን መረጠ፡፡ ምንም እንኳን የቃል ኪዳን እስረኛ ቢሆንም፣ የእርሱ ነፃ ፈቃድ መግለጫ ሆኖ መዝለቁ ግን ፈፅሞ አይለወጥም፡፡ [ዶ/ር ፖል ቻንግ፣ ትርጉም]*

ለዳዊት በገባው ቃል ኪዳን ምክንያት፣ ሕዝቡን ለማዳን ሰብዓዊ መሲህ ለመላክ ራሱን ግዴታ ውስጥ አስገባ፡፡ ያም መሲህ ኢየሱስ ነበር፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ለህዝቡ የማስተሰረያ መስዋዕት ሊሆን የሚችለው የዳዊት ልጅ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 14 እስከ 17 መሲሁ ሰው ሊሆን እንደሚገባው ያመለክተናል፡፡ ከዚያም ባሻገር ኢሳያስ ምዕራፍ 53 ስርየት በዳዊት ልጅ ብቻ ሊከናወን እንደሚገባ ተጨማሪ መስፈርቶችን ይጨምርልናል፡፡

መሲሁ ሰው ሊሆን የተገባበት ሦስተኛው ምክንያት ዳግማዊው አዳም መሆን ስላለበት ነው፡፡ ያም፣ አዳም በወደቀበት ስፍራ እርሱ ድል ሊነሳ ይገባዋል ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር፣ አዳም የፍጥረት ሁሉ የበላይ እንዲሆን አደረገ፣ የሰውንም ዘር ዓለምን ወደ እግዚአብሔር መንግሥትነት ይለውጥ ዘንድ ሾመው፡፡ አዳም ግን በደለ፣ የሰውንም ዘር የኃጢአት ሰለባ አደረገው፣ የተሰጠንንም አደራ መወጣት የማንችል ደካሞች አደረገን፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ይህንን ታሪክ የምናገኘው ሲሆን፣ ሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 19 ደግሞ ወሳኝነቱን በጥልቀት ያብራራልናል፡፡ የብሉይ ኪዳኖቹ የታሪክ መጻሕፍት፣ የወደቀው የሰው ዘር ለረጅም ምዕተ-ዓመታት የአግዚአብሔርን መንግሥት ለመመሥረት ሲሞክር ግን ሳይሳካለት ሲቀር መዝለቁን መዝግበውልናል፡፡

አሁንም ቢሆን የአብ መሻት አልተለወጠም፡፡ ማለትም ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት የመገንባት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ስለዚህም፣ በመጨረሻ አብ ይህንን ችግር ያቃልል ዘንድ አንድያ ልጁን ላከ፡፡ ልጁም መንግሥትን ለእኛ ሊመሠርት መጣ፡፡ ግን በእኛ ምትክ ለመገንባትም ሆነ የእኛን ስፍራ ለመውሰድ እርሱ ራሱ ሰው ሊሆን ይገባዋል፡፡ ጽድቅን በተሞላ ሕይወቱ፣ በስርየታዊ ሞቱ፣ በኃይል በመነሣቱ እና በሰማያት በመንገሡ፣ አዳምና እኛ ሁላችን በወደቅንበት ኢየሱስ ድል ነሳልን፡፡ እርሱ የሰው ዘር ሁለተኛው አዳም ሆነ፡፡ ስለዚህ እኛ በእምነት ከኢየሱስ ጋር አንድ ስንሆን፣ የእርሱ ድል የእ6ኛ፣ የእርሱም ኃይል የእኛ ብርታት ይሆነናል፡፡ እኛም ወደ ከበረው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ግንባታ ሃላፊነታችን በክብር ተመለስን፡፡

ስለ ኢየሱስ ሰውነት ባደረግነው ጥናት፣ ልዩ ልዩ ሰብዓዊ ልምምዶቹን ተመልክተናል፣ ደግሞም እንደ መሲህነቱ ወይም ክርስቶስነቱ ያለውን ሰብዓዊ አገልግሎት ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ የኢየሱስ ሰብዓዊ ተፈጥሮ ከመለኮታዊ ተፈጥሮው ጋር ስላለው ግንኙነት እንነጋገራለን፡፡

# ተፈጥሮ

ኢየሱስ ሰዋዊ ስብዕና አለው ስንል፣ ሰው መሆን የሚገለጥባቸው የባሕርይ መገለጫዎችና ፈተናዎች ሁሉ አሉት ማለታችን ነው፡፡ እነርሱም ሰዋዊ አካል እና ነፍስ ናቸው፡፡

በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመናት ሁሉ፣ በርካታ የነገረ-መለኮት ምሁራን በክርስቶስ ሰብዓዊነት ላይ ብርቱ ጦርነት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ እርሱ ሙሉ በሙሉ ሰው ነበርን? እውነተኛ ሥጋ እና ደም ያለው አካል ነበረው፣ ወይስ እንዲያው ሰው መስሎ ተገለጠ? እውነተኛ የሰው ነፍስ ነበረው፣ ወይስ መለኮታዊ ስብዕናው ባዶ አካል ተዋሰ? እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎች እንዲያው ቴክኒካዊ እና ማስጢራዊ፣ እንዲያውም አላስፈላጊ ሊመስሉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ወቅቶች በክርስቶስ ሰብዓዊ ተፈጥሮ ላይ የሚደረጉ ሙግቶች ቤተክርስቲያንን እስከ መከፈል የሚያደርሱ ፈተናዎች ሆነዋል፡፡ ለበርካታ የነገረ-መለኮት ጉባኤዎች የመነጋገሪያ ርዕሶች የነበሩ ሲሆን፣ ለበርካታ የሃሰት ትምህርቶችም የማደናቀፊያ ዐለት ሆነው ኖረዋል፡፡ ዛሬም እንኳን የክርስቶስን ሰብዓዊነት በተዛባ መንገድ የመረዳቱ ጉዳይ ለወንጌል ዝቅተኛ ስፍራ እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ ስለዚህ፣ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ቢያንስ የክርስቶስን ስብዕና መሠረታዊ ገፅታዎች የመረዳቱ ነገር ወሳኝ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ተአማኒ የሆነው ክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት ኢየሱስ በሁሉም ገፅታ ሰው መሆኑን በፅኑ በማስረገጥ ይፀናል፡፡ ማለትም እርሱ አካልም ነፍስም የነበረው መሆኑን፤ ህማም፣ አደጋና ሞት የገጠመው መሆኑን፤ እንደሁላችን በሰውነቱ ውሱንነት የነበረው መሆኑን እናሌሎችም ማለት ነው፡፡

ስለ ኢየሱስ ይህንን ስንነጋገር፣ ምስሉ ብዙም ሳይቆይ ይመሳቀልብን ይጀምራል ምክንያቱም ኢየሱስ በጣም ወሳኝ በሆኑ ጥቂት ጉዳዮች ከሌሎች ሰብዓዊ ፍጡራን የሚለይባቸው ማንነቶች ነበሩትና ነው፡፡ አንዱን ብናነሳ፣ ኢየሱስ ፍፁም ሰው ነበር፣ ሌሎቻችን ግን ብዙ እንከኖች አሉብን፡፡ ይህም በመካከላችን የማይናቁ ልዩነቶች መኖራቸውን ያሰየናል፡፡ ለምሳሌ፣ ሁሉም የአዳም ዘር ኃጢአትን ሠርቷል፡፡ ይህንንም በ1 ነገሥት ምዕራፍ 8 ቁጥር 46፣ መዝሙር ምዕራፍ 130 ቁጥር 3፣ መዝሙር 143 ቁር 2፣ ሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 12፣ ገላትያ ምዕራፍ 3 ቁጥር 22 እና በሌሎችም በርካታ ምንባቦች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ አንዱን ለምሳሌ ብንወስድ፣ በሮሜ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 10 እስከ 12 ያለው እንዲህ ይደመጣል፡

> እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ።
> ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥
> በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም።

ኢየሱስ ግን ልዩ ነው፡፡ ያለ ኀጢአት ተወለደ፣ ከኀጢአት የነፃ ሕይወትም ኖረ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእርሱን ኀጢአት አልባ ሕይወት በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 14 እና 15 እና ምዕራፍ 9 ቁጥር 14 በመሳሰሉት ምንባቦች ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ እንግዲያው፣ ይህንን ሃሳብ

ኢየሱስ እውነተኛ ሰብኣዊ ተፈጥሮ ነበረው ከሚለው ድምዳሜ ጋር እንዴት እናስታርቀዋለን? መልሱ በቀላሉ፣ የኀጢአት ተልዕኮ እና እንዲያውም ኀጢአትን የማድረግ አቅም ለሰውነት ወሳኝ ነገሮች አይደሉም የሚል ይሆናል፡፡

ገና ከጅማሬው እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሲፈጥር ኀጢአትን ከማድረግ አቅም ጋር የፈጠረው መሆኑ እውን ነው፡፡ ይህንንም በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 አዳምና ሔዋን መልካምንና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ በበሉ ወቅት አረጋግጠውታል፡፡ ግን አንድ ልንቀበለው የሚገባ እውነት ቢኖር ከመበደላቸውም በፊት ሰዎች የነበሩ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲያው፣ ሰው ሆኖ ኀጢአትን አለመሥራት ይቻላል ማለት ነው፡፡

ኢየሱስን ልዩ የሚያደርገው ሁለተኛ ነገር ሁለት ማንነቶች ማለትም፣ ሰብዓዊነትና መለኮትነት ያሉት ብቸኛ ሰው መሆኑ ነው፡፡ የተቀረው የሰው ዘር ሁሉ አንድ ተፈጥሮ ብቻ ነው ያለው፡፡ ያም ሰብዓዊ ተፈጥሮ ነው፡፡ ኢየሱስ ግን አምላክም ሰውም ነው፣ ማለትም በአንድ ጊዜ ፍፁም ሰው ፍፁምም አምላክ ነው ማለት ነው፡፡

ግን ልብ ልንለው የሚገባ ነገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ሁለት ተፈጥሮዎች እንዴት በማንነቱ ውስጥ እንደተዋሃዱ እንድ በአንድ የማያስረዳን መሆኑን ነው፡፡ ይህንን ጥምረት ለማብራራት በቀላሉ አለመቻሉም በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ በርካታ ክርክሮችን አስነስቷል፡፡ በስተመጨረሻው ግን የቀደመችው ቤተክርስቲያን የክርስቶስን አንድ ማንነትና ሁለት ስብዕና አጣምሮ በያዘ አንድ ቃል ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚሰጡት ፍቺ ባልተዛነፈ መንገድ በመፍታት ነገሩን መስመር አስያዘችው፡፡

በክርስቶስ ስብዕና ውሰጥ የሚገኙትን ሰዋዊና መለኮታዊ ማንነቶች ለመግለጥ አገልግሎት ላይ የዋለው ቃል “ hypostatic union/ በአማርኛችን ፍፁም ሰው ፍፁምም አምላክ” የሚል ነው፡፡ ለዘመናዊው አድማጭ ነገሩ እንግዳ ቢመስልም፣ በቀደመችው ቤተክርስቲያን እንዴት አገልግሎት ላይ እንደዋለ ስናስብ እንረዳዋለን፡፡ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን፣ “hypostasis” የሚለው ቃል ስብዕና ብለን በተለምዶ የምንጠቀምበትን ቃል፣ በተለይም የስላሴን ስብዕና ለመግለጥ የሚውል ቃል ነበር፡፡

ለምሳሌ፣ The Holy Spirit በተሰኘው *ሥራው* ምዕራፍ 18 ላይ፣ የአራተኛው ክፍለ ዘመን አባት የነበረው ባሲል ሃይፖስትሲስ የተሰኘውን ቃል እንዲህ ተጠቅሞበታል፡

> *አንድ እግዚአብሔር አብ፣ አንድ አንድያ ልጅ (ወልድ) እና አንድ መንፈስ ቅዱስ አለ፡፡ እያንዳንዳቸውንም ማንነተቶች በአንድ ማንነት እናውጃለን፡፡*

በዚህ ስፍራ፣ ባሲል እያለ ያለው እኛ "እያንዳንዳቸውን ማንነቶች በምሉዕ አንድነታቸው እናውቃለን" ከምንለው ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ነው ፍቺውን የሚያስቀምጠው፡፡ ስለዚህ የሃይፖስታቲክ ዩኒየን አስተምህሮ፣ መለኮታዊና ሰብዓዊ ማንነቶች ስለተዋሃዱበት አንድ አምላክ ወይንም ስለ እግዚአብሔር ወልድ እንዲህ በግልፁ ያስቀምጣል፡:

> *ኢየሱስ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ፣ ሁለቱም ማንነቶች የየራሳቸው የባህርይ መገለጫ ያሉዋቸውን (መለኮትነትና ሰውነት) የያዘ አንድ አካል ነው፡፡*

እግዚአብሔር ወልድ ዘወትር ሁሉንም የባህርይ መገለጫዎች ፍፁም መለኮትነትን ይዞ ይኖራል፡፡ በሰውነት ሲፀነስና ሲወለድ ደግሞ፣ የሰውን ዘር ወሳኝ ባህርያት አካልና ነፍስ በማንነቱ ላይ ጨመረ፡፡

በአዲስ ኪዳን ይህንን የሃይፖስቴቲክ አንድነት የሚገልፁ ክፍል ፊሊጵስዩስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 5 እስከ 7 ያለው ሲሆን፣ ጳውሎስ እንዲህ ጽፎታል፡-

> … እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር
> መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥
> ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥
> (ፊልጵ 2፥5-7)

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ኢሱስ አምላክ መሆኑንና ምሉዕ መለኮትንት እንዳለው ግልፅ አድርጓል፡፡ ከዚያም፣ *ሥጋ ሆነ* ማለትም በነበረው መለኮታዊ ተፈጥሮ ላይ ሰብዓዊ ተፈጥሮን ጨመረ፡፡ "ራሱን ባዶ አደረገ" በማለት ጳውሎስ የሰጠው መግለጫ አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖችን ግራ ያጋባቸዋል፡፡

አንዳንዶች በተሳሳተ መንገድ ኢየሱስ ክብሩን ወደዚያ ዘወር አደረገው ወይንም እንዲያውም መለኮትነቱን ተወው ብለው ያስባሉ፡፡ ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንደተመለከትነው፣ ይህ ሊሆን ፈፅሞ አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር ማንነት አይለዋወጥም፡፡ እግዚአብሔር የእርሱን ወሳኝ ባህርያት ወደ ጎን ሊላቸው አይችልም፣ ምሉዕ ማንነቱን እንደዚሁ፡፡

እንደ እድል ሆኖ፣ ጳውሎስ የዚህ ሐረግ ፍቺ በሁለት ከግስ በሚፈጠሩ ሐረጎች፡ የባሪያን መልክ በመያዝ ሰው መሆኑን በማብራራት ግልፅ አድርጎታል፡፡ እነዚህ ሐረጎች ኢየሱስ እንዴት "ራሱን ባዶ እንዳደረገ" ይነግሩናል፡፡ በተለይም፣ ኢየሱስ ራሱን ባዶ ያደረገው መለኮትነቱን በመጣል ሳይሆን፣ ሌላ ተፈጥሮ በመጨመር ነው፣ ያም ሰውነት ሲሆን ሰውነቱ ግን መለኮታዊ ክብሩን እንዲጋርድ አድርጎታል እንጂ መለኮትነቱን አልተካም ፡፡

በዚህ ረገድ የሃይፖስቴቲክ አንድነትን በሚገባ ያብራራው በ451 ዓ.ም. (እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር) በትንሿ እስያ ሰሜናዊ ክፍል በኬልቄዶን ከተማ ተሰብስቦ የነበረው የዓለም ሃይማኖቶች ጉባኤ ባወጣው የሃይማኖት መግለጫ ላይ ነው፡፡ የኬልቄዶኑ ጉባኤ የተገናኘው ለትውፊታዊው የክርስቶስ ስብዕናና ተፈጥሮ ሊሟገትለትና ይህንን አስመልክቶ የነበሩትን ኑፋቄዎች ወግዱ ለማለት ነበር፡፡

ጉባኤው ያወጣው አንቀጽ *የኬልቄዶን የሃይማኖት መግለጫ* ወይንም "ዓርማ" እና *የኬልቄዶን ማብራሪያ* የሚሉትን ጨምሮ በተለያዩ መጠሪያዎች ይታወቃል፡፡

> *ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክና ፍፁምም ሰው ነው፤ እውነተኛ አምላክ እውነተኛም ሰው፣ በነገር ሁሉ ከኃጢአት በስተቀር እንደኛው የሆነ.... ነፍስና አካል ያለው በሁለቱ ተፈጥሮዎቹ ውስጥ ሊታወቅ የሚገባው፣ ያለማምታታት፣ ያለመለዋወጥ፣ ያለመከፋፈልም የፍጥረቶቹም የየራሳቸው ማንነት ከአንድነቱ በምንም ምክንያት ሊነጣጠሉ የማይችል፣ የእያንዳንዳቸው ስብዕናዎች ተፈጥሮ ግን በራሱ የተጠበቀ እና በአንድ ስብዕና በአንድ ማንነት የተዋሃዱበት ነው፡፡*

የኬልቄዶኑ የሃይማኖት መግለጫ ቋንቋ በአብዛኛው ቴክኒካዊ ነው፡፡ በሁለት ነጥቦች ግን ልናጠቃልለው እንችላለን፡፡ በአንድ በኩል፣ ኢየሱስ አንድ ብቻ ነው፡፡ ልክ ፍጥረታዊው ሰው መለኮታዊ ማንነትን በውስጡ እንዳካተተ ዓይነት ሁለት ማንነቶች ወይንም ልቡና የለውም፡፡ አሊያም ደግሞ መለኮታዊ ስብዕና ከፍጥረታዊው ስብዕና ጋር እንደተቀላቀለበት ዓይነት፣ የሁለት የተለያዩ ስብዕናዎች ቅልቅል ወይንም ድቅል የሆነ አንድ ስብዕናም አይደለም፡፡ እርሱ ለዘወትር ዘላለማዊው እና የእግዚአብሔር ልጅ ብለን የምናውቀው ነው እንደሆነም ይኖራል፡፡

በተመሳሳይም፣ ኢየሱስ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ተፈጥሮዎች አሉት፡ መለኮትነትና ሰውነት፡፡ ልክ የአብ ተፈጥሮ ምሉዕ መለኮት እንደሆነ ሁሉ እና ልክ የሰዎችም ተፈጥሮ ምሉዕ ሰውነት እንደሆነ ሁሉ፣ የእርሱም ተፈጥሮዎች ምሉዕና ፍፁም ናቸው፡፡ ኢየሱስ ለመለኮትነት የማይቀነሱ ባህርያትን ለሰውነትም የማይቀነሱ ባህርያትን ይዟል፡፡

ከዚህ ባሻገር፣ የኢየሱስ ሁለት ተፈጥሮዎች የየራሳቸው ማንነት ያላቸው ናቸው፡፡ እርሱ የመለኮትን እና የሰውን ባህርይ ያዳቀለ ድቅል ተፈጥሮ የለውም፡፡ የእርሱ ሰዋዊ ባህርያት መለኮታዊ ባህርያቱን አያደናቅፉም ወይም መለኮታዊ ባህርያቱ ሰብዓዊ ባህርያቱን ለየት አያደርጉም፡፡ እያንዳንዱ ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ አይለወጤ ነው፡፡

> *እንደ እንደማስበው ለዕብራውያን የተጻፈው ደብዳቤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚሆነው መካከለኛ፣ ታላቁ ሊቀ ካህን፣ ፍፁም ሰው ፍፁምም አምላክ እንዴት ሊሆን እንደሚገባው ያጠቃለለበት መንገድ አሳቻ ይመስላል፡፡ እርሱ በሥልጣኑ ቃል ዓለማትን*

*ሁሉ የፈጠረና የሚያጸናቸው ዘላለማዊ አምላክ ነው፡፡ እርሱ ፍፁም አምላክ ነው፡፡ ከዚያ በመቀጠልም ዕብራውያን፣ ፍፁም ሰው የሆነ ሊቀ ካህን ስለሚያስፈልገን ስለ እኛ፣ ልክ እንደ እኛ በደምና በሥጋ ተካፈለ፡፡ ስለዚህም ወንድማችን ነው፡፡ ሰውነታችንንም ስለተካፈለ ስለ እኛ ይማልድልናል፣ በፍፁም መታዘዝም መከራንና ስቃይን ተቀበለ እናም እንደ ሰው መፈተን ምን እንደሚመስል ያውቃል፡፡ ስለዚህም ወንድማችን የሆነ ሊቀ ካህን ያስፈልገናል፡፡ በተጨማሪም ለዘላለም የሚኖርና የሚማልድልንም መለኮታዊ ሊቀ ካህን ያስፈልገናል፡፡ እናም ያንን በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ አገኘነው፡፡ [ዶ/ር ዴኒስ ጆንሰን]*

እንደ እርሱ ተከታዮች ከመኖር አንፃር የክርስቶስ ሰውነት በርካታ አንድምታዎች አሉት፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5 እንደጻፈው፣ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የሆነ ፍፁም ሰው የሆነ አስታራቂ አለ፣ በእርሱም ሞት ምክንያት ይቅርታን በማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ በሙሉ እንደታረቁ ልጆች እንኖራለን፡፡ እንደገናም ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 19 እንደሚያስተምረን፣ ልክ ሁለተኛው አዳም፣ ኢየሱስ በእርሱ በሚታመኑት በእነርሱ አዲስን የሰው ዘር እንደፈጠረ ሁሉ፣ በፍጥረታት ላይ ወደ ነበረን ክብርና የላቀ ስብዕና መልሶናል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ እኛ አሁን እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኙ መንገዶች እንኖራለን፣ አልፎም ዓለምንም ልክ ሰማያዊቱን መንግሥቱን እንድትመስል እንለውጣለን፡፡ ስለዚህም እያንዳንዳችን በግል፣ በሕይወታችን ከኀጢአትና ከመከራ ጋር ስንታገል፣ ፍፁም ሰው የሆነውም አዳኛችን ድካማችንንና ስቃያችንን እንደሚገባውና እንደሚራራልን፣ ስቃያችንንም ለማቅለል፣ ባህርያችንንም ለመቅረፅ እና ዘላለማዊ ብድራታችንን ለማብዛት ፈጥኖ እንደሚመልስልን በማወቅ በእምነት ወደ ፀጋው ዙፋን ልንቀርብ፣ ይገባል፡፡ የክርስቶስ ሰውነት በሕይወታችን ያሳደረውን ተፅዕኖ ከሚገልጡ ተቆጥረው ከማያልቁ መንገዶች መካከል ጥቂቶቹ እኚህ ናቸው፡፡

በትምህርታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትነትና ሰውነት ለመዳሰስ ሞክረናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ወደ ተገለጠው የክርስቶስ ሥራ እንሸጋገራለን፡፡

# 4. ሥራ

ላለፉት ጥቂት መቶ ምዕተ-ዓመታት፣ የነገረ-መለኮት ሊቃውንቱ ስለ ኢየሱስ ሥራ በሁለት ሃሳቦች ላይ መወያየታቸው የተለመደ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመጀመሪያ፣ መዋረዱ አለ፣ ማለትም የወደቀውን የሰው ዘር ለመቤዠት እንዴት አድርጎ የሰውን ደካማ ተፈጥሮ ለመካፈል ዝቅ እንዳለና በምድር መከራን ለመቀበል እንደተዋረደ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የእርሱም መከበር አለ፣ ማለትም እግዚአብሔር አብ እንዴት አድርጎ የእርሱን የተሰወረ ዘላለማዊ ክብር

እንደገለጠና፣ ክብርን እንዴት እንደጨመረለት ማለት ነው፡፡ እነዚህ ጎራዎች በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ቃል በቃል አልተቀመጡም፣ ሆኖም ስለ ኢየሱስ ሥራ ለማሰብ ጠቃሚ መንገዶች ናቸው፡፡

በዚህ ትምህርት የኢየሱስን ሥራዎች ስንመለከት፣ በመጀመሪያ መዋረዱን እንመለከታለን፣ ማለትም ክብሩን ሸፈን ከለል ያደረጉ ነገሮችን ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ መከበሩን እንመለከታለን፣ ማለትም ክብሩን የገለጡትንና ወደ ፊትም ከዚህም በላቀ የሚገለጠውን ክብሩን ማለት ነው፡፡ አስቀድመን በምድር አገልግሎቱ የታየውን የክርስቶስን መዋረድ በመመልከት እንጀምር፡፡

# መዋረድ

ኢየሱስ በመዋረዱ የሠራቸው ሥራዎች በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ከታች በተገለጡት መስመሮች ተቀምጠዋል፡

> በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፣
>
> ከድንግል ማርያም በተወለደ፡፡
>
> በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣
>
> በተሰቀለ፣ በሞተ እና በተቀበረ፤
>
> ወደ ሲዖልም በወረደ፡፡

በእነዚህ ሥራዎች፣ የእግዚአብሔር ልጅ ክብሩ ከዕይታ እንዲሸፈን አደረገ፣ ራሱንም ለመከራና ክብር ለማጣት አሳልፎ ሰጠ፡፡ ምክንያቱም የወልድ መለኮታዊ ተፈጥሮ ስለማይለዋወጥ፣ ሊዋረድ አይችልምና፡፡ ስለዚህ፣ መዋረዱ በሰብዓዊ ማንነቱ የተወሰነ ነው፡፡ ይህም ሆኖ፣ ሰውነቱ ከስብዕናው ጋር በፍፁም የተዋሃደ ስለሆነ፣ መለኮታዊ ስብዕናው የመዋረዱ ምሉዕ ተካፋይ ሆኗል፡፡

በዚህ ትምህርት፣ ኢየሱስ በመዋረዱ የሠራቸውን ሥራዎች በሁለት ርዕሶች ጠቅለል እናደርጋቸዋለን፡፡ እነርሱም ትሥጉቱና ህማማቱ፡፡ በመጀመሪያ በትሥጉቱ፣ ማለትም ወደ ምድር ሰው ሆኖ በመምጣቱ እንጀምር፡፡

# ትሥጉት

"ትሥጉት" የሚለው ቃል ኢየሱስ በዘላቂነት ሰው መሆኑን የሚያመለክት ነገረ መለኮታዊ ቃል ነው፡፡ የቁም ፍቺውም፣ "ትሥጉት" ማለት "ሥጋ መሆን" የሚለውን ያመለክታል፣ ያም የሰው

አካል ነው፡፡ እንደተመለከትነው ግን፣ ኢየሱስ የሰው ነፍስም እንዳለው የክርስቲያን ነገረ መለኮት ዘወትር አጥብቆ ይሟገታል፡፡ ስለዚህ በነገረ-መለኮት ስለ ትሥጉት ስንናገር፣ በጥቅሉ ስለ ኢየሱስ ጥቅል ሰውነት መናገራችን ነው ማለት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ትስጉት በበርካታ ስፍራዎች ይናገራሉ፣ ለምሳሌ፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 14፤ ፊሊጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 6 እና 7 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 14 እስከ 17፡፡

ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 14 ምናልባትም "ትሥጉት" ለተሰኘው ቴክኒካዊ ቃል ምንጭ ሳይሆን አይቀርም፡፡ እስኪ ዮሐንስ በዚያ የጻፈውን አድምጡ፡

> በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።... ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ (ዮሐ 1፥1፣14)

ዮሐንስ የተናገረውን አስተውሉ የእግዚአብሔር ልጅ "ሥጋ ሆነ" ነው ያለው ይህም የትሥጉት የቁም ትርጉሙ ነው፡፡ ነጥቡም ኢየሱስ እውነተኛውን ሰውነት ያዘ፣ ያም እውነተኛ አካልንም የሚጨምር ነው፡፡

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ፣ ከኢየሱስ ትስጉት ጋር የተያያዙት ሥራዎች መፀነሱና መወለዱ ናቸው፡፡ ቀደም ብለን ስለ ኢየሱስ ትውልድ ስንናገር ስለነዚህ ሁነቶች ተነጋግረናል፣ የሰው ልጅነቱንም እንደሚያረጋግጡ አይተናል፡፡ አሁንም፣ እነዚህኑ ሁነቶች እናነሳለን፣ ግን ከኢየሱስ የመሲህነት ሥራዎች አንፃር ይሆናል፡፡ ትሥጉት ለምን አስፈላጊ ሆነ? ኢየሱስስ በዚያ ምን አሳካ?

ቅዱሳት መጻሕፍት የኢየሱስ የትሥጉትነት ሥራዎች ቢያንስ ሦስት ነገሮችን እንዳከናወኑ ያስተምሩናል፡፡ በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ወልድ ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ የመሆንን ሕጋዊ መብት ይሰጠዋል፡፡ ሁለተኛ፣ የተዋጣለት ሊቀ ካህን ለመሆን የሚችልበትን ምህረትና እኛን መሳይነት ያላብሰዋል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ኢየሱስ የኃጢአት መስዋዕት መሆን ይችል ዘንድ ትሥጉት አስፈላጊ ነበር፡፡

እነዚህን ነጥቦች በዝርዝር እንመልከታቸው፣ ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ የሰው ዘር ሊሆን የተገባው መሆኑን እናስቀድማለን፡፡

እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ መሲሁ የሰው ልጅ ሊሆን እንደተገባው ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ አሁን፣ የኢየሱስ የትስጉትነት ሥራ በዳዊት ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ኢየሱስን እንዴት እንዳስቻለው እንመለከታለን፡፡ አሁን ከፊታችን የሚደቀነው ችግር የዳዊትን ዙፋን ለመውረስ የሚችሉት ልጆቹ ብቻ የመሆናቸው ነገር ነው፡፡ እንግዲያው፣ ዮሴፍ

ማርያምን ሲያገባትና ኢየሱስን ልጁ አድርጎ ሲወስድ፣ ኢየሱስ የዮሴፍ ዝርያ የመሆን ሕጋዊ መብት አግኝቷል በዚያም መሲሃዊ ንጉሥ ይሆን ዘንድ መብትን አግኝቷል፡፡

ትሥጉትነቱ ለኢየሱስ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ እንዲሆን ሕጋዊ ባለመብት ከማድረጉ ባሻገር፣ ለሕዝቦቹ ሊቀ ካህን ለመሆን የሚችልበትን ምህረትና እኛን መሳይነት እንዲላበስ አስችሎታል፡፡

*የኢየሱስ ትሥጉት በደካማነት ስሜታችን የተነካ ሊቀ ካህን እንዲሆን እንዳደረገው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ይህም ማለት ሰው መሆንን በሙላት ሳይቀምስና ከእኛ ጋርና ስለእኛ መከራን ሳይቀበል ሊሰማው ከሚችለው ይልቅ የተዋጣለት ሊቀካህን እንዲሆን አድርጎታል ማለት ነው፡፡ ይህም የተከናወነባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ልክ እኛ እንደሚገጥመን ሁሉ ኢየሱስም በዚህ በወደቀው ዓለም ውስጥ የሚገኝ ሰው ሊገጥመው የሚችለውን ሰብዓዊ ችግር በሕይወት ዘመኑ ቀምሷል፣ እግዚአብሔር በትስጉት በዚህ በወደቀው ዓለም የሚኖር ሁሉ የሚገጥመውን የልብ ስቃይ፣ ሃዘን፣ መከፋት፣ መከዳት እና መቁሰልን ቀምሷል፡፡ ይህም ለእርሱ እንዲያው ባዶ ፅንሰ ሃሳብ፣ በቀላያት ጥልቅ ውስጥ ራቅ ብሎ ቆሞ፣ ዘላለም በሚባልም አይዘጌ አቧራ ውስጥ ወዲያ ርቆ እንዲህ ሊሰማቸው ይችላል ብሎ የሚናገረው ነገር አይደለም፡፡ እርሱ ራሱ በምስኪኑ ሥጋችን፣ በምስኪኑ ደማችን ተካፍሎ ወደ ዓለም በመምጣት ያጣጣመው ነገር ነው፡፡ [ዶ/ር ጂ. ሊጎን ዱንካን ሣልሳዊ]*

የዕብራውያን ፀሐፊም ይህን የትስጉትነት ገፅታ በዕብራውያን ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 እና 18 ላይ አውስቶታል፡፡ እስኪ በዚያ የጻፈውን አድምጡ፡

> ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።
> እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና። (ዕብ 2፥17-18)

ኢየሱስ ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ፣ የተዋጣለት ሊቀ ካህን እንዲሆን መብት ከመስጠቱ ባሻገር፣ ትስጉቱ ለህዝቡ የኀጢአት መስዋዕት እንዲሆንም አስችሎታል፡፡

ቀደም ብለን በዚሁ ትምህርት፣ ኢየሱስ በህዝቡ ምትክ ይሞት ዘንድ ሰው ሊሆን እንደሚገባው ተመልክተናል፡፡ ግን ለስርየት ለምን ሰው መሆን አስፈለገ? መልሱ ለሰው ኀጢአት እግዚአብሔር የበየነው ሰዋዊ ሞት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን በዘፍጥረት 2 ቁጥር 17፣ ሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 12 እና ምዕራፍ 6ቁጥር 23፣ ያዕቆብ ምእራፍ 1ቁጥር 15 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች ያስተምሩናል፡፡ ከአዳም ጀምሮ በሰው ዘር ሁሉ ላይ ኀጢአት ተስፋፋ፣

የሰብዓዊ ሞትን ሕጋዊ ፍርድም አመጣ፡፡ የእግዚአብሔርን መስፈርት ሊያሟላ የሚችለው የእውነተኛ ሥጋና ደም ሰብዓዊ ሞት የሆነው ለዚህ ነው፡፡

ጳውሎስ በሮሜ ምእራፍ 5 ከቁጥር 15 እስከ 19 በኢየሱስ ሰውነትና በእኛ ድነት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት እንዳብራራው አድምጡ፡

> ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።
> አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኩነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ።
> በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።
> እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።
> በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። (ሮሜ 5፥15-19)

ጳውሎስ እየደጋገመ የሚያነሳው፣ የኢየሱስ ሰዋዊ ጽድቅ ለአዳም ሰዋዊ ኀጢአት ማርከሻና መድኃኒት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በሰፋ መንገድ ጳውሎስ ግልጽ የሚያደርገው አዳም ያበላሸውን ለማቅናት ኢየሱስ ሰው ሊሆን ተገብቶታል በማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር በሰው ዘር ላይ የጣለውን ቅጣት ለመቀበልና ለተቀረውም የሰው ዘር ጽድቁን ለማደል ሰው መሆን ነበረበት፡፡

> *አንዳንድ ጊዜ እኛ እንደ ወግ አጥባቂ ወንጌል አማኝ ክርስቲያንነታችን፣ በክርስቶስ መለኮትነት ላይ አፅንኦት እንሰጣለን ስለዚህም የዳንንበትን ሰውነቱን ችላ እንላለን፡፡ ኢየሱስ እውነተኛ የሰው ዘር በመሆኑ ምክንያት፣ ስለ እኛ መከራ ሊቀበልና ስለ ኀጢአታችንም ሊሞት ችሏል፡፡ ስለዚህ፣ የኢየሱስ ሰውነት ለእኛ መዳን እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ]*

ይህን የኢየሱስን ትስጉት መረዳት በልቡናችን ይዘን፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተጠቀሰውን ሁለተኛውን የመዋረዱን ገፅታ ህማማቱን እንዳስሳለን፡፡

# ህማማት

“ህማማት” የሚለው ነገረ-መለኮታዊ ቃል pascho ከተሰኘው የግሪክ ግሥ የተወሰደ ነው፡፡ የሚያመለክተውም ከተያዘባት ምሽት አንስቶ ያለፈበትን የኢየሱስ መከራና ሞት ነው፡፡ የኢየሱስ ህማማት በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እንዲህ ተጠቅሷል፡

*በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ፣*

*በተሰቀለ፣ በሞተ እና በተቀበረ፤*

*ወደ ሲኦልም በወረደ፡፡*

አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ የመያዝ፣ የመከራና የመሰቀል ታሪክ ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ስለ እነዚህ ነገሮች ዝርዝር ከመመልከት ይልቅ፣ ኢየሱስ ለእነዚህ ሁነቶች ራሱን ያስገዛበትን ምክንያት እንመለከታለን፡፡

ከኢየሱስ መከራ አንፃር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ መታዘዝን ይማርና ለእግዚአብሔር አብ ራሱን ያስገዛ ዘንድ አስፈላጊ ነው ብለው ያብራራሉ፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 5 ቁጥር 8 እንዲህ ተጽፏል፡

ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ (ዕብ 5፥8)

ጴጥሮስም በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2ቁጥር 20 እና 21 ላይ እንደጻፈው፡

ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሡ፥ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፥ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል።
የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። (1ጴጥ 2፥20-21)

ኢየሱስ በመከራው የአባቱን ፈቃድ ፈፀመ፣ በዚያም ራሱን ለአባቱ አቀረበ፡፡ አባቱንም ፈፅሞ በመታዘዙ፣ የዘላለም ብድራትን ተቀበለ ያንንም አሁን በጸጋው ለእኛ አካፍሎናል፡፡

ክርስቶስ በጲላጦስ የደረሰበት ፈተና በመከራ ብቻ አላበቃም፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ፡፡ እንደ አውነቱ በኢየሱስ መዋረድ ከተሠሩት ሥራዎች በበጎ ምክንያት ከሁሉ ይልቅ የሚታወቀው ይህኛው ነው፡፡ ለኀጢአታችን ስርየትን ያገኘነውና ደነታችንም የተፈፀመው በሞቱ ነው፡፡

*የኢየሱስ ለኀጢአት መሞት (በአዲስ ኪዳን በጠቅላላው የተገለጠው እንዲሁ ነው) ተሳክቷል፣ ምክንያቱም እርሱ የቅጣታችን ምትክ ሆኖ መጥቷልና፡፡ "ምትክ" ማለት የእኛን ስፍራ ወስዷል ማለት ነው፣ "ቅጣት"ደግሞ የሚያመለክተው እርሱ እኛ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመተላለፍ ያመጣነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ በመቀበል በመቀበል ፍርዳችንን በመሸከም፣ ቅጣታችንን በመቀጣት የእኛ ምትክ ሆነ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ተፈጥሮው፣ ማለቴ እንደ እውነቱ የቅድስና ባሕርዩ ይህ ነው፣ ይህም ኀጢአት ባለበት ቦታ ሁሉ አፀፋው ደግሞ አለ ማለት ነው፡፡ እጅግ አስደናቂ የሆነውና ፍቅርን የተሞላው እግዚአብሔር ያቀደው የድነት ዕቅድ የእኛን ቅጣት ከበደለኞቹ ትከሻ ላይ በማንሳት በደል አልባ እና ንፁህ በሆነው አንድያ ልጁ ትከሻ ላይ ጫነው በዚያም እርሱ በብሉይ ኪዳን ይቀርብ የነበረው የንፁሕ እንስሳ መስዋእት ሙላት ሆነ፡፡ [ዶ/ር ጄ. አይ ፓከር]*

ሐዋርያው ጳውሎስ ስቅለት የወንጌል ልብ መሆኑን ደጋግሞ ገልጧል፡፡ ይህንንም ሮሜ ምዕራፍ 6 ቁጥር 6፣ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 17 እና 18፣ ገላትያ ምዕራፍ 6 ቁጥር 14 እና ቆላስያስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 20 በመሳሰሉት ስፍራዎች እንመለከታለን፡፡ ከነዚህም አንዱን በመውሰድ፣ ገላትያ ምዕራፍ 2 ቁጥር 20 እና 21 ያለውን አድምጡ፡

> ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም
> ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና
> ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው
> ነው።
> የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ
> ክርስቶስ በከንቱ ሞተ። (ገላ 2፥20-21)

የክርስቶስ ሞት ድነታችን የተፈፀመበት ማዕከላዊ ሥራ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በታሪክ ዘመናት ሁሉ እርሱ የወንጌል መልዕክቶች ማዕከል ሆኖ ዘልቋል፡፡

ከስቅለቱ በኋላ፣ የኢየሱስ አካል በመቃብር ውስጥ ለሦስት ቀናት ሕይወት አልባ ሆኖ ተቀብሮ ቆየ፡፡ ፍፁም ሰው በመሆኑ፣ ኢየሱስ ሰብዓዊ ሞትን ቀመሰ፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ይህንን እውነታ ወደ ሲዖል ወረደ ብሎ መዝግቦታል፡፡ በዚህ ወቅት፣ የኢየሱስ አካል በመቃብር ውስጥ ሲቆይ ነፍሱ ግን ሙታን ወዳሉበት ወረደች፡፡

ዘመናውያኑ የነገረ-መለኮት ምሁራን "ወደ ሲዖል በወረደ" የሚለውን ሐረግ ፍቺ ሙሉ በሙሉ አይስማሙበትም፡፡ ዛሬ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን መስመር ኢየሱስ መቀበሩን ብቻ ያመለክታል ብለው ይፈቱታል፡፡ ግን የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ሊያስተላልፍ የሚፈልገው ትርጉም ይህ እንዳልሆነ ግልፅ ይመስላል፡፡

አንዱ ነገር፣ የሃይማኖት መግለጫው ኢየሱስ መቀበሩንና ወደ ሲዖልም መውረዱን ገልጧል፡፡ ለየትኛውም ክስተቶች፣ እነዚህ ሐረጎች ራሳቸውን የቻሉና በታሪክ ምዝገባው ውስጥ ተከታታይነት ያላቸው ናቸው፡፡

ሌላኛው ነገር ደግሞ፣ "ሲዖል" የሚለው ሐረግ በቀላሉ "ከመሬት በታች" የሚል ፍቺ እንዳለው እውነት ቢሆንም፣ በቅዱሳት መጻሕፍትና በቀደምቷ ቤተክርስቲያን ጽሑፎች በአብዛኛዎቹ የሚያመለክተው የሙታን ነፍስ የሚኖርበትን ታችኛውን ዓለም ነው፡፡ ይህም የቀደምቷ ቤተክርስቲያን የማይዘነጋ ፍቺዋ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን ማለትም የጥንት ክርስቲያኖች "ሲዖል" የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ በአዕምሯቸው የሚኖራቸው ፍቺ ማለት ነው፡፡

በነዚህም ምክንያቶች፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ሊያስተምር ዓላማ ያደረገው በሞቱና በትንሣኤው መካከል ባለው ጊዜ የኢየሱስ ነፍስ ወደ ታችኛው ዓለም ወርዳለች የሚለውን መሆኑን መደምደም የተሻለ ነው፡፡ የዚህ ሲዖል ተፈጥሮ ምንድን ነው?

በጥንታዊው ዓለም፣ ፍጥረተ ዓለም የሚገለጠው አብዛኛውን ጊዜ በአቀብዮሽ ቀጥተኛ አወቃቀር ነው፡፡ ሰው የሚኖርባትም ምድር በመካከል ናት፡፡ እግዚአብሔርና መላእክቱ የሚኖሩበት መንግሥተ ሰማይ፣ በሰማይ ላይ አለ ተብሎ ይነገራል፡፡ ከመሬት በታች ደግሞ የሙታን ነፍሶች የሚኖሩበት ጨለማ ታችኛ ዓለም አለ፡፡ በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን፣ በተለምዶ የሚጠራው sheol ተብሎ ነው፤ በአዲስ ኪዳኑ የግሪክ ቅጂና በብሉይ ኪዳኑ የግሪክ ትርጉም hades ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ (አማርኛችን ለሁሉም የሚጠቀመው ሲዖል የሚለውን መሆኑን ልብ ይሏል፡፡)

በብሉይ ኪዳን፣ በጎም ይሁን መልካም የሠሩ ነፍሶች እስከ መጨረሻው የፍርድ ቀን ድረስ በዚያ ይኖራሉ ተብሎ ይነገራል፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን ሲዖል፣ በሉቃስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 15 እንደተጠቀሰው በአብዛኛው የሚያመለክተው የክፉዎች ነፍሳት መኖሪያ ተደርጎ ነው፡፡ ሆኖም ግን፣ ቢያንስ ከኢየሱስ ትንሣኤ በፊት፣ አዲስ ኪዳንም የጻድቃንም ነፍስ በሲዖል እንደ ነበር አረጋግጧል፡፡ በአብዛኛው እንደሚጠቀሰው፣ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 27 እስከ 29 ጻድቁ ንጉሥ ዳዊት በሲዖል እንደ ነበረ ይናገራል፡፡

ይህ ማለት ግን ሁሉም በሲዖል ያሉ ሁሉ እኩል ይታያሉ ማለት አይደለም፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 16 ከቁጥር 19 እስከ 31፣ ኢየሱስ ስለ ዓላዛርና ስለ ባለጠጋው ሰው በተናገረው ምሳሌ እንደተገለፀው በጻድቃንና በክፉዎች ነፍሶች መካከል ትልቅ ገደል በመካከል አለ፡፡ ክፉዎች በእሳት ሲሰቃዩ፣ ጻድቃን ግን በምቾት ይኖራሉ፡፡ በዚህ ምሳሌ፣ አብርሃም በምቹው ስፍራ ተቀምጧል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የነገረ መለኮት ምሁራኑ ይህንን የታችኛው ክፍል ወገን "የአብርሃም ወገን" ወይንም በቁም ትርጉሙ "የአብርሃም እቅፍ" ብለው ይጠሩታል፡፡

የቤተክርስቲያን አባት የሆነው ተርቱሊያን፣ በሦስተኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ እንደ ጻፈው፣ ከዚህ የታችኛው ክፍል ወገን አንጻር የተለመደ የእምነት አቋም አስፍሯል፡፡ On the Resurrection of the Flesh በተባለው ጽሁፉ ምዕራፍ 17 ላይ የጻፈውን አድምጡ፡

*ነፍሶች አሁን እንኳን በሲኦል ገሚሶቹ ለእሳት ገሚሶቹ ደግሞ ለበረከት የተጠበቁ መሆኑን የዓልዓዛር ታሪክ አረጋግጧል፡፡*

እንደገናም የቤተክርስቲያን አባት የሆነው ኢግናቲየስ፣ በ107 ዓ.ም በጻፈውና ለትራላውያን በጻፈው መልእክቱ ይህ ብሏል፡

*ከመሬት በታች ያሉት፣ ማለቴ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚናገሩት "አንቀላፍተው የነበሩ ቅዱሳን አካላት ተነሥተው ታዩ" ከጌታ ጋር የተነሡት በርካቶች፣ መቃብሮቻቸው ተከፍተው ነበር፡፡ እርሱ ወደ ሲኦል ብቻውን ወረደ፣ ግን በበርካቶች ታጅቦ ተነሣ፤ ከዓለም ጅማሬ ጀምሮ በነበረው መለየት ተለየ፡፡*

እንግዲያው የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ኢየሱስ ወደ ሲኦል ወረደ ሲል፣ ከሁሉ የሚቀርበው ትርጉም የእርሱ ሰብዓዊ ነፍስ ከአካል ወደ ተለዩ መንፈሶች ወረደች ማለት ነው፡፡ በተለይም፣ ለጻድቃን ነፍሶች ወደ ተዘጋጀው ስፍራ ወረደ ማለት ነው እንጂ ለከፉዎች ወደ ተዘጋጀው የስቃይ ስፍራ አይደለም፡፡ የኢየሱስ በዚህ የሲኦል ክፍል የመቆየቱ ነገር ወሳኝነት ያለው የሥራው ክፍል ነው ምክንያቱም ነፍሱ ለሰብዓዊ ፍጡራን በተመደበላት ፍትሃዊ ቅጣት ውስጥ ማለፍ ነበረባትና ነው፡፡

የኢየሱስ ህማማት በወደቀው ዓለም ውስጥ በእውነት ሰው ሆኖ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያሳያል፡፡ እንግዲያው ይህ አንከን የሌለበት የእኛ ጌታ ለኃጢአት መድሃኒት ይሆን ዘንድ መከራን ከተቀበለ፣ እኛማ ንፁህን ያልሆንነው ምንኛ መከራ ልንቀበል ይገባን? ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 12 እንደጻፈው፣ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወድዱ ሁሉ መከራ አይቀሬ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን ግን፣ እኛ ስንሰቃይ ክርስቶስም ይሰቃያል፡፡ ይህም ማለት የእኛ ህመም ይሰማዋል ስለዚህም ሊያጽናናን ዝግጁ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ በቆላስያስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 24 እንዳስተማረው፣ በስተመጨረሻ የክርስቶስ መከራ በእኛ ፍፁም ይሆናል፡፡ ያም ከሆነ በኋላ፣ እርሱ በክብር ይመለሳል እኛም ዘላለማዊ ሃብታችንን እንወርሳለን፡፡ መከራችን ዓላማ የለሽ አይደለም፤ እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለሙን በጠቅላላ ወደ ምሉዕ ኅዳሴ የሚያመጣበት መሣሪያው ነው፡፡

ኢየሱስ በመዋረዱ ያከናወነውን ሥራ ከተመለከትን፣ የእርሱን መከበር ደግሞ መመልከታችን አስፈላጊ ነው፣ ያም አንድ ጊዜ እንደገና የእርሱ መለኮታዊ ክብር በሚገለጥበት ጊዜ የሚሆነውን ማለት ነው፡፡

# መክበር

ስለ ክርስቶስ መክበር ስንነጋገር፣ ነገሩ ተጋርዶ የነበረውን ክብር ከመግለጥ የሚዘልል ነገር መሆኑን ማስተዋል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመዋረዱ፣ ወልድ አስቀድሞ ከነበረው ክብር ይልቅ የሚበልጥ ክብርን ተቀብሏል፡፡ አብ የባረካቸውን ሥራዎች ሠርቷል፣ በመሰዋቱም ሰዎችን የገዛ ርስቱ አድርጎ ገዝቷል፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋን ላይ የመቀመጥንም መብት አግኝቷል፡፡ በእነዚህም ሥራዎች፣ ወልድ ክብር የተገባው ሆኗል በመዋረዱም እጅግ በዝቶለታል፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የክርስቶስን መክበር በሚከተሉት አንቀፆች ገልጦታል፡-

*በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሥቷል፡፡*

*ወደ ሰማይ አርጓል*

*ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል፡፡*

*ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ይመለሳል፡፡*

የክርስቶስ መለኮታዊ ተፈጥሮ መቼም ቢሆን ላይለዋወጥ የከበረ ነው፡፡ ሊሞት አይችልም፣ በሰማያት ካለው ዙፋኑም ሊወገድ አይችልም፡፡ እንግዲያው፣ የእግዚአብሔር ወልድ መክበር ለሰብዓዊ ተፈጥሮው ነው ማለት ነው፡፡ አሁንም ግን፣ ልክ ክርስቶስ በሌሎቹ ሰብዓዊ ልምዶቹ እንደሆነው ሁሉ፣ የእርሱ መለኮታዊ ስብዕናም የመክበሩ ተካፋይ ነው፡፡

በክርስቶስ መክበር ላይ የምናደርገው ውይይት አራት ክፍሎች አሉት፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ክርስቶስ ከሞት መነሣት እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ወደ ሰማይ ስለማረጉ እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ፣ በአብ ቀኝ በዙፋን ላይ የመቀመጡን ፍቺ እንመረምራለን፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ ወደፊት የሚሰጠውን ፍርድ እናነሳለን፡፡ አሁን በተሰቀለ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ስለ መነሣቱ በመመልከት እንጀምር፡፡

# ትንሣኤ

የክርስቶስ ትንሣኤ የሞቱን ያህል ለመዳናችን ወሳኝ መሆኑን በርካታ ክርስቲያኖች አይረዱም፡፡ 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 21 በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ስለመዳን የሚናገረው ለዚህ ነው፡፡ አያችሁ፣ ምንም እንኳን ደጋግመን የምንለው እንደዚያ ቢሆንም መዳናችን እንዲያው ክርስቶስ በእኛ ፈንታ ገዝቶ ያመጣውና እንካችሁ ብሎ እንደ ስጦታ የሰጠን የሆነ ነገር አይደለም፡፡

ይልቁኑ ከእርሱ ጋር በመተባበራችን የምንቀበለው ስጦታ ነው፡፡ ይህም በአዲስ ኪዳን መልእክቶች ደጋግመን የምንሰማው "በክርስቶስ" የመሆን ሃሳብ ነው፡፡

በእርሱ ሞት ምክንያት ይቅር ተብለናል ምክንያቱም፣ ከእርሱ ጋር በመተባበራችን በመስቀል ላይ ከእርሱ ጋር ተሰቅለናልና፡፡ በእርሱም ትንሣኤ እኛም በአዲስ ሕይወት በመነሣታችን የዘላለምን ሕይወት አግኝተናል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ነገር በሮሜ ምዕራፍ 6 ከቁጥር 3 እስከ 11 እና ምዕራፍ 8 ቁጥር 10 እና 11፣ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 14 እና ምዕራፍ 13 ቁጥር 4፣ ቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 11 እስከ ምዕራፍ 3 ቁጥር 3 እና በሌሎችም በርካታ ቦታዎች ይናገራሉ፡፡ አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት ያህል፣ ጳውሎስ በምዕራፍ 6 ቁጥር 4 እና 5 እነዚህን ቃላት ጽፏል፡

> እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም
> በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ
> በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።
> ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል
> ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ (ሮሜ 6፥4-5)

በአጭሩ፣ ክርስቶስ ከሞት በመነሣቱ የሠራው ሥራ ባመንን ወቅት እኛም አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት መቀበላችንን ያረጋገጠ ሲሆን፣ ይህም ወደፊት ልክ እንደ እርሱ በትንሣኤ የምንቀበለውን የከበረ አካል ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ፣ የእርሱ መከበር ወደ ከበረ ማንነታችን የምንመለስበት ክብራችን ነው፡፡

> *ኢየሱስ በሞቱ ከኀጢአት ኃይል በስቲያ ተቀመጠ፡፡ የሞተን ሰው ልትፈትኑት አትችሉም፡፡ ከዲያቢሎስ ሃይልም በስቲያ ተቀመጠ፡፡ ኀጢአት ግን ከእርሱ ኀይለኛ ባላጋራ ጋር እንዲጋጠም አደረገው፡፡ ሞትን ፊት ለፊትም ሲጋጠመው ኢየሱስ ሞትን ድል ነሣ፡፡ የዚህም ነገር እንድምታው ለሕዝቦቹ አስደናቂ ነው፡፡ ስለዚህም፣ በራዕይ ምዕራፍ አንድ ቁጥር ዐሥራ ስምንት፣ ኢየሱስ ከሞት የተነሣው የከበረው ክርስቶስ፣ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ። ሲል አውጇል፡፡ ራሱን ነፃ ለማውጣት ተጠቅሞባቸዋል፣ ግን ደግሞም አንድ ቀን የገዛ ሕዝቡን ከሞት ባርነት ነፃ ለማውጣት ይጠቀምባቸው ዘንድ እነዚህን ቁልፎች መልሶ ጠብቋቸዋል፡፡ [ዶ/ር ኖክስ ቻምብሊን]*
>
> *መስቀልና የኢየሱስ ትንሣኤ የኀጢአትን ይቅርታ የተቀበልንበት፣ ኀጢአታችን የተሰረየበት ብቻ ሳይሆን ከዚያም የላቀ ምናልባትም እጅግ የላቀ ጠቀሜታ ባለው መንገድ፣ ትንሣኤ የዓለም አዲስ ዘመን የተጀመረበት ነው፡፡ አዲሱ ፍጥረት (ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚጠሩት) በመቃብር፣ በዚያ ባዶ መቃብር ውስጥ ተጀመረ፡፡ ያም በእውነት አዲሱ*

*የትኩረት ነጥብ ነው፣ ማለትም የታሪክ የራሱ አዲስ መዘውር ነው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት እኛ ሁላችን አሁን የምንኖረው በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ነው፡፡ እርሱም የፍፃሜውን መጀመሪያ በይፋ አውጇል፣ የክርስቲያኖችም ተስፋ የፍፃሜው ጅማሬ በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ሙላቱን የማግኙ ነገር ነው፣ ይህም ቅዱሳት መጻሕፍት አዲስ ፍጥረት ብለው የሚጠሩት ነው፡፡ [ዶ/ር ጆናታን ፔኒንግተን]*

ከትንሣኤውም በተጨማሪ፣ የኢየሱስ መከበር ከምድር ወደ ሰማይ ማረጉንም ያካትታል፡፡

## ዕርገት

ዕርገት ኢየሱስ በአካል ወደ ሰማይ የተወሰደበት ሁነት ነው፡፡ ከትንሣኤው አርባ ቀናት በኋላ፣ ኢየሱስ በደመና ወደ ሰማያት አረገ፡፡ ሉቃስ ዕርገትን በሉቃስ 24 ቁጥር 50 እና 51 እና በሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 1 ከቁጥር 6 እስከ 11 ገልጦታል፡፡

የኢሱስ ዕርገት እርሱ እስከ ዛሬ በምድር ቢኖር ሊያከናውናቸው የማይችላቸውን በርካታ ነገሮች እንዲያከናውን አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ፣ በዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 2 እና 3 ላይ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በሰማያት ስፍራ ሊያዘጋጅላቸው እንደሚሄድ ነግሯቸዋል፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 7 ላይ፣ ወደ ሰማያት አስቀድሞ ካልሄደ ቤተክርስቲያንን ለአገልግሎት ለማስታጠቅ መንፈስ ቅዱስን እንደማይልክላቸውም ነግሯቸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ በመስቀል ላይ የጀመረውን የስርየት ሥራ ወደ ሙላት ለማምጣትም ኢየሱስ ወደ ሰማያት ማረጉ ግድ ነበር፡፡ የዕብራውን ጸሐፊም ይህንን መሟገቻውን በመጽሐፉ ምዕራፍ 8 እና 9 ላይ ያቀርባል፡፡ ጠቅለል ስናደርገውም፣ ምድራዊቷ መቅደስ የሰማያዊቷ ጥላ ናት ይላል፡፡ ይህንንም የክርስቶስን የማስተሰረይ ሥራ በዓመት አንድ ጊዜ ከሚከናወነው ከምድራዊው ካህን የማስተሰረይ ሥራ ጋር፣ ማለትም የመስዋዕቱን ደም በተቀደሰው ስፍራ በመውሰድ በመሰዊያው ላይ በመርጨት ለሕዝቡ የኀጢአትን ስርየት ከማስገኘታቸው ጋር ያነፃፅረዋል፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ ኢየሱስ በሰማያት በእውነተኛዋ መቅደስ ወደምትገኘው ታላቅና ፍፁም ድንኳን ገባ፣ በመሰዊያውም ላይ የራሱን ደም ረጨ፡፡ ይህም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የጀመረውን ሥርዓት ወደ ሙላት አመጣው፡፡

ዕብራውያን ምዕራፍ 9 ቁጥር 11 እና 12 በሰማያት የሚከናወነውን የክርስቶስን የማስተሰረይ አገልግሎት እንዴት እንደገለጠው አድምጡ፡

ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ፥ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን፥

> የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም። (ዕብ 9፥11-12)

ከዚያም ባሻገር፣ በሰማያት እንዳለ ሊቀ ካህናችን፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ይማልድልናል፣ ማለትም ኀጢአትን በምንሠራ ወቅት ስለ እኛ ስርየት የከፈለውን በማሳየት ዘወትር ይማልድልናል፡፡ የነገረ-መለኮት ምሁራኑ በሰማያት ክርስቶስ የሚያከናውነውን የማያቋርጥ *ሥራ* በተለምዶ የእርሱ ሰሞን (ለካህኑ ዘካርያስ በክፍሉ ተራ የተባለለትን ያመሳክሯል) በማለት ይጠቅሱታል፡፡ የእኛን ድነት የተረጋገጠ የሚያደርገው ይህ ተራው ነው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 24 እና 25 የእርሱን ተራ በዚህ መንገድ ይገልጠዋል፡

> እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። (ዕብ 7፥24-25)

በዚህ ስፍራ እንደምንመለከተው፣ የኢየሱስ ወደ ሰማይ ማረግ ለቤዝዎት *ሥራ*ው ወሳኝ ገፅታ አለው፡፡ ያለዚያ አንድንም ነበር፡፡

የክርስቶስን ትንሣኤና ዕርገት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በሰማያት በእግዚአብሔር ቀኝ በዙፋን ስለመቀመጡ እንነጋገራለን፡፡

## ንግሥና

አዲስ ኪዳን የኢየሱስን በአብ ቀኝ በዙፋን መቀመጥ በበርካታ ስፍራዎች ያነሳል፡፡ መሠረታዊው ሃሳብ ኢየሱስ ታላቁ ንጉሣችን፣ በአብ ታላቅ ዙፋን ቀኝ የሚቀመጥበት ዙፋን በሰማይ ያለው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ትዕይንት፣ አብ ታላቅ ንጉሥ፣ ወልድ ደግሞ ከእርሱ ጎን እርሱን የሚያገለግል ንጉሥ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህም በቀደሙት ዘውዳዊ አገዛዞች ውስጥ፣ ትናንሾቹ ነገሥታት በዋናው ግዛት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የግዛቱን ክፍሎች ከሚገዙበት እና ለንጉሠ ነገሥቱ ከሚገብሩበትና አገልግሎት ከሚሰጡበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል፡፡

> *ስለ ክርስቶስ ንግሥና ስናስብ፣ በመደበኛነት የምናስበው እጅግ ከፍ ባለ ስፍራ ከፍ ማለቱን፣ በእግዚአብሔር አብም ቀኝ ከመቀመጡም የተነሳ ንጉሥ መሆኑን ነው፡፡ ግን ኢየሱስ በንግሥናው የከበረው በሰብዓዊ ማንነቱ መሆኑን ማስታወስ አለብን፡፡ ኢየሱስ በሰማይና በምድር ሥልጣን የተሰጠው በሰውነቱ ነው፡፡ ማለትም፣ በመለኮታዊ ተፈጥሮው፣ ኢየሱስ ዘወትር ንጉሥ ነው፡፡ በሁሉም ላይ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው በመሆኑ*

*ዘወትር ገዢ ነው፡፡ ኢየሱስ የዳዊት ልጅ ነው፣ እርሱም እስራኤልን ወይንም የእግዚአብሔርን ህዝብ የሚወክል ነው፡፡ የዳዊትም ልጅ፣ ልክ እንደ ዳዊት ሁሉ፣ ሎሌ ንጉሥ ነው፤ ላታላቁ ንጉሥ፣ በሰማያት ለሚኖረው ለእግዚአብሔር አብ አገሊጋይ ነው፡፡ [ዶ/ር ሪቻርድ ፕራት ትንሹ]*

ኢየሱስ በንጉሥነት በተጠቀሰበት ምንባብ፣ ስለ ህዝቡ የሚማልድም ካህን መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ይህም የቀደሙት ነገሥታት ለህዝባቸው እንደ ካህን ያገለግሉ የነበረበትን ተምሳሊት ይከተላል፡፡ ለምሳሌ፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 14 መልከጼዴቅ ንጉሥም ካህንም ነበር፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ በአብ ቀኝ ስላለው ስፍራ ሲናገሩ፣ አንዳንድ ጊዜ የሚያተኩሩት የእኛ መሲሃዊ ንጉሥ በመሆኑ ሃላፊነቱ ላይ ነው፡፡ ይህም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 30 እስከ 36፤ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 18 እስከ 23፤ በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 3 እስከ 9 እና በ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 21 እና 22 ላይ እንደተጠቀሰው ነው፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስን ሃላፊነት ስለ እኛ የሚማልድ ሊቀ ካህን አድርጎ በአፅንኦት ያስቀምጠዋል፡፡ ይህንንም እንደ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 34 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 8 ቁጥር 1 ላይ እናገኘዋለን፡፡

በሁለቱም፣ ትርጉሙ ተመሳሳይ ነው፡፡ ኢየሱስ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሥልጣንና ኀይል አለው፣ በአባቱም ምትክ ሆኖ ይገዛል፡፡ በዚያም ሥልጣኑ፣ ለህዝቦቹ ድነትን አስገኝቷል፣ አብም በሞገሱ እንደሚያስባቸው ዋስትና ሰጥቷል፡፡

የኢሱስን ከሞት መነሣት፣ ወደ ሰማይ ማረጉን እና በአብ ቀኝ በንግሥና መቀመጡን ካወሳ በኋላ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው በመጨረሻው ቀን ክርስቶስ ስለሚበይነው ፍርድ ይጠቅሳል፡፡

# ፍርድ

የሃይማኖት መግለጫው ኢየሱስ ለፍርድ ይመለሳል ሲል፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ካለው ዙፋኑ፣ ከዚያ የሚመጣ መሆኑን መግለጡ ነው፡፡ ሃሳቡም ኢየሱስ በፍጥረት ሁሉ ላይ የሚገዛው ንጉሥ፣ ንግሥናውንና መንግሥቱን ባልተቀበሉና ሕግጋቱን ባፈረሱት ላይ ንጉሣዊ ፍርድ ሊበይን የሚመጣ መሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ሉቃስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 30፤ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ቁጥር 31 እና 2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ቁጥር 5 እና ምዕራፍ 4 ቁጥር 1 ላይ እናገኘዋለን፡፡

የመጨረሻው ፍርድ በምድር ላይ የኖረውን እያንዳንዱን ሰው ሕያዋንንም ሆነ ሙታንን፣ ኢየሱስም ሲመጣ በሕይወት ያሉትንም ሁሉ ያካትታል፡፡ የእያንዳንዱ ሰው የተነገረች

እያንዳንዲቱ ቃልና ተግባር እንደ እግዚአብሔር ባህርይ ይፈረድባታል፡፡ እጅግ ዘግናኝ የሆነው እውነታ እያንዳንዱ ሰው በኀጢአቱ በደለኛና ሞት የተመደበለት ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡

የምሥራቹ ግን በእምነት ከክርስቶስ ጋር የተባበሩት አስቀድሞውኑ በክርስቶስ ሞት በፍርድ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው በክርስቶስ ትንሣኤ ነፃ ወጥተዋል፡፡ ስለዚህም፣ በፍርድ ቀን፣ የዘላለም በረከትና ውርስ ይቀበላሉ፡፡

አሳዛኙ ዜና ግን በክርስቶስ ያልሆኑት የእግዚአብሔርን የነደደ ቁጣ በራሳቸው ሰውነት ላይ ይሸከማሉ፡፡ ለዘላለምም ወደ ሲዖል ይጣላሉ፡፡

> *አሁን በእኛ ዘመን የመጨረሻው ፍርድ አስተምህሮ እምብዛም አይታወቅም፡፡ ነገሮች በፍፁም አይለወጡም፣ የፍርድ ነገር ሰዎችን በፍፁም ይማርካል ብዬም አላስብም፡፡ እኔ ግን ስለ ፍርድም የመናገሩ ነገር ለድርድር የማይቀርብ ወሳኝ ነገር ነው ብዬ እሚገታለሁ፡፡ እምነታቸውን በክርስቶስ ያላደረጉ ሁሉ የዘላላም እሳት እንደሚጠብቃቸው ልናውጅ ይገባል፡፡ [ዶ/ር ቶም ሽሬነር]*

> *ስለ ሲዖል ልንናገር የሚገባበት አንዱ ምክንያት እውን በመሆኑ ነው፡፡ እውነትንም ልናመልጥ አንችልም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግማሽ እውነቶች፣ አሊያም ዘጠና በመቶ እውነቶች ይነገራሉ፣ በበቂ ሁኔታ ወንጌልን እናድርስ ከተባለና በእውነትም ወንጌልን የምናደርስ ከሆነ ስለማይቀረው ፍርድ መናገር ይገባናል፡፡ ስለ ሲዖል እንናገራለን ያም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለ ሲዖል ልንገነዘበው የሚገባው አንዱ ነገር ፈራጁ ማን እንደሆነ የሚያሳስበን መሆኑ ነው፡፡ እኛ ሳንሆን፤ እርሱ ነው፡፡ ስለ ግል ሃላፊነታችን ያሳስበናል፡፡ ስለ አጣዳፊነቱ ያሳስበናል፡፡ ስለ ዘላለምም ያሳስበናል፡፡ ስለዚህ ሲዖል ወደ እኛ ይዞ የሚመጣው በርካታ ነገር አለ፣ ስለዚህ ሲዖልን ቀንሶ ወንጌልን ለማድረስ መሞከር እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ ስለ እርሱ እንነጋገራለን፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ስለ ሲዖል የምንነጋገርበት ምክንያት እውነት ስለሆነና ከእውነትም ልንሸሽ ስለማንችል ነው፡፡ [ዶ/ር ማት ፍሬድ ማን]*

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩትን የእምነት አንቀፆች ዳስሰናል፡፡ መለኮታዊ ተፈጥሮውንና ከስላሴ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ጨምሮ የእርሱን ፍፁም መለኮትነት አይተናል፡፡ በተጨማሪም በመለኮትነቱና በሰውነቱ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች አካትተንም ፍፁም ሰውነቱን ዳስሰናል፡፡ ከመዋረዱ አንስቶ እስከ ምሉዕ ክብሩ ድረስ ያለውን ሥራውንም ጠቅለል አድርገን አይተናል፡፡

ራሳችንን ክርስቲያኖች ብለን ለምንጠራውም ሆነ፣ ክርስትናን ለመረዳት ለሚሹ ሁሉ፣ ስለ ክርስቶስ ስብዕናና ሥራ የተጨበጠ ነገር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ኢየሱስ የሃይማኖታችን ማዕከል ነው፡፡ ከሌሎች የእምነት ተቋማት የለየን ያ ስብዕና ነው፡፡ እርሱ የፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ ገዢ ነው የታሪክም መዘውር በእርሱ እጅ ነው፡፡ እርሱ አምላካችን፣ ሊቀ ካህናችን እና ንጉሣችን ነው፡፡ ድነትም እርሱን ከማወቅ፣ ከመውደድ እና ከእርሱም ጋር አንድ ከመሆን የዘላለምንም ሕይወት ከማግኘት ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡